www.ethiopianorthodox.org

# እግዚአብሔርን መፍራት

የእስክንድርያው ፓትርያርክ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ እንደጻፉት

ተርጓሚ
መምህር ሰሎሞን በቀለ
የወልደነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስና
የመካነ ጎልጎታ ቅድስተ ማርያም ቤ/ክ
ዋና ጸሐፊ

አዲስ አበባ
2001 ዓ.ም (2009)

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ


መቅደም ........ 1
መግቢያ ........ 2

ምዕራፍ አንድ
ለምን እግዚአብሔርን ስለመፍራት እናወራለን? ........ 4
ስለዚህ ለምን ስለፍርሃት እናወራለን? ........ 4

ምዕራፍ ሁለት
የፍርሃት ምንጮች ........ 13
የመጀመሪያው አይነት ፍርሃት የመውደቅ ፍርሃት ነው ........ 13
የፍርድ ወይም የኃጢአትን መዘዝ መፍራት ከኃጢአት ጋር
የተያያዘ ፍርሃት ነው ........ 17
ኃጢአተኛ ሁለት አይነት ቅጣቶችን ይፈራል
ምድራዊና ሰማያዊ ........ 17

ምዕራፍ ሦስት
እግዚአብሔርን የመፍራት ጥቅሞች ........ 21

ምዕራፍ አራት
እግዚአብሔርን መፍራት በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ........ 32
የታዋቂ ኃጢአተኛ ታሪክ ........ 34
የእግዚአብሔር ቤት ቅዱስነት ........ 35
ሌሎች የቤተ ክርስቲያን እርምጃች ........ 36

ምዕራፍ አምስት
እግዚአብሔርን መፍራት እንዴት ማግኘት ይቻላል? ........ 38
ከእግዚአብሔር መለየት አያስፈራችሁምን?
ከእርሱ ተለይቶ በጨለማ ውስጥ መኖርስ? ........ 39
እግዚአብሔርን መፍራት ታላላቆቻችንን በማክበር
እናገኘዋለን ........ 63
እግዚአብሔርን መፍራት በጸሎት ወቅት ለእግዚአብሔር
ክብር እንድትሰጥ ያደርጋል ........ 70
እግዚአብሔርን ወደመፍራት ለመድረስ የሚሠሩ ልምምዶች ........ 74

ምዕራፍ ስድስት
ፈሪሃ እግዚአብሔር ከፍቅሩ ይመጣል አብሮትም ይቀጥላል ........ 81
ፈሪሃ እግዚአብሔርም ቢሆን ያለእናንተ መገኘት አይችልም ........ 87

ምዕራፍ ሰባት
ፍቅርና ፍርሃት ........ 89
በታላቅ የአክብሮት ስሜት እግዚአብሔርን መፍራት ........ 89
እግዚአብሔርን የማሞገስ ትርጉሙ ምንድን ነው? ........ 91

ምዕራፍ ስምንት
ተቃውሞና ማስተባበል ........ 95

www.ethiopianorthodox.org

# መቅደም

ከዚህ በፊት በጻፍኳቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ርህራሄው እና ምሕረቱ በሚሉት መጻህፍቶች መሐከል ሚዛን ስመጠበቅ ስል ይህን መጽሐፍ ለማሣተም ምኞቱ ነበረኝ። እንዲያውም «ፍቅር» በሚለው ቀደም ሲል ባሳተምኩት መጽሐፍ በመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ ላካትተው ነበር። ነገር ግን በሁለት ምክንያቶች ለብቻው ላሳትመው ፈለኩ። 1ኛ/ የራሱ የሆነ ትኩረት እንዲያገኝ እና በሌላ የመጽሐፉ ምዕራፎች ገብቶ እንዳይጠፋ 2ኛ/ ፀፀት በሚል ርዕስ ስር ከጻፍኳቸው መጽሐፍቶች አንዱ እንዲሆን ነው። በዚህ ርዕስ የፀፀት ሕይወት፣ መንፈሳዊ ዕይታ እና መንፈሳዊ ሕይወትን ነቅቶ መጠበቅ የሚሉ ሦስት መጽሐፍቶችን ጽፌያለሁ። ይህ እግዚአብሔርን መፍራት የሚለው ደግሞ አራተኛው መጽሐፌ ነው።

ፖፕ ሺኖዳ ሣልሳዊ

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ፈሪሃ እግዚአብሔርን ትተው ፍቅሩን ብቻ ጠበቅ አድርገው የያዙ ሰዎች አሉ:: እግዚአብሔርን መፍራት ፍቅረ እግዚአብሔር መሆኑን ሳይረዱና በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ሳያጤኑ ነው:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማግኘት መጨረሻው ደግሞ ፍቅሩ ነውና:: ይህም ቅዱስ መጽሐፋችን ሲያረጋግጥልን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ምሳ 9÷10 ይለናል::

እግዚአብሔርን በመፍራት ውስጥ ለትዕዛዙ መገዛትን እንማራለን፣ ለፍቅሩ እንበረከካለን፣ በፀጋው እናድጋለን፣ ከቅዱሳኑ ኅብረት ጋር እንደመራለን:: ስለሆነም እግዚአብሔርን በመፍራት ውስጥ የራሱ የሆነ የምናገኛቸው ጥቅሞች ይኖሩናል:: ጥቂቶቹ በዝርዝር እንመልከት:-

1. ለንስሐና ለሕጉ ወደ መገዛት ይመራናል፣
2. በመንፈሳዊ ሕይወት ቆራጥ ያደርገናል፣
3. ወደ ትህትናና ወደ ተሰበረ ልብ ይመራናል፣
4. በራሳችን ኃጢአት ላይ እንድንፈርድ ያደርገናል፣
5. ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌላው ማሰብ እንለምድበታለን::

እነዚህን አትኩረን ከተመለከትናቸው:: እግዚአብሔርን በመፍራት የምናገኛቸው ጥቅሞች ሲሆኑ፣ በመጽሐፉ ላይም የበለጠ ዳብረው ተብራርተዋል:: እግዚአብሔርን መፍራት ማናችንም በደል እንዳንፈጽም ይጠብቀናል:: ሐናኒያና ሰጲራ በዋሹ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲገስጻቸው ወዲያውኑ ሞቱ:: ይህንን



መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:: «በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ» የሐ.ሥራ5÷11:: ይህ ፍርሀት ብዙዎችን ከኃጢአት ቆጥቧል::

ቅዱስ ጳውሎስ ጠንቋዩ ኤልማስን እውር እንዳደረገው እናስታውሳለን:: (የሐዋ.ሥራ 13÷11) «ሌሎች ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሰሩትን በሁሉ ፊት ገስጻቸው» 1ኛ ጢሞ 3÷20 በማለት የመንፈስ ልጁን ጢሞቴዎስን መክሮታል::

እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮችን ስንመለከት ፈሪሀ እግዚአብሔር ካለ ሰዎች ሁሉ ወደ ለየለት ስህተት እንዳይወድቁ ይጠብቃቸዋል:: ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ ይላል:- «የኔ ወንድም ስራዎችህ አንተ ላይ ከመፍረዳቸው በፊት አንተ ራስህ ላይ ፍረድ» በማለት ፈረሀ እግዚአብሔር እራሳችንን እንድንመረምር መንገድ ይከፍትልናል::

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ በዚህ መጽሐፋቸው ላይ የማይጠገቡ ብዙ ቁም ነገሮችን ለማስጨበጥ የሞከሩ በመሆኑ ይህን መጽሐፍ በማንበብ ጠቃሚውን የሕይወት ኑሮ እንድ ትይዙ እጋብዛለሁ::

መምህር ሰሎሞን በቀለ (B.Th)
2001 ዓ.ም / 2009 G.C
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አንድ

## ስምን እግዚአብሔርን ስለመፍራት እናወራለን?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ርህራሄ እና ፍቅር በማስተማር ላይ ሳለ እግዚአብሔርን ስለመፍራት ማውራት አንድን ሰው ሊያስገርም ይችላል:: ሰዎች በምህረትና በርህራሄ ስለሚንከባከቡንና ኃጢአታችንን ስንናዘዝ ይቅር ስለሚለን መሀሪና መልካም አምላክ ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ሁልጊዜ ስናወራ መስማታቸው የተለመደ ነው::

## ስለዚህ ለምን ስለፍርሃት እናወራለን?

መልሱ ሁለት አይነት ሰዎች ስላሉ ነው:: በፍቅር በጣም የሚጠቁና ቸልተኛ ለመሆን ፍቅርን የሚጠቀሙ:: ልባቸው በፍቅር የሚጠቃ ሰዎችም ሁለት አይነት ናቸው:: እግዚአብሔርን የሚወዱና እንደ ሀሳቡ የሚመላለሱ ባላቸው ኃይል በሙሉ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር በሕይወታቸው በባህሪያቸው እና ለእግዚአብሔር ባላቸው መታዘዝ የተገለፀ ነው:: የልባቸውም መሻት ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር የተስማማ ነው:: ይህ ነው ተስማሚው. . .፤ ነገር ግን ሁሉም ሰዎች እንደዚህ አይደሉም:: እግዚአብሔርን የሚወዱ ነገር ግን ፈቃደኝነትንና በተግባር ላይ ማዋልን የሚያጡም አሉ:: ፍቅር በልብ ላይ እንጂ በእጅ ላይ እንዳለ ማህተም አይደለም መኃልየ



8:6፤ ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስ ከሞት በተነሣ ጊዜ ሲክደው እንዲህ አይነት ሰው ነበር:: «ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው» (ዮሐንስ 21:17) ጌታን ሲክደው ፍቅር እንጂ ፍርሀት አልነበረበትም ቅዱስ ጴጥሮስ ከጌታ ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት ሰዎችን ይፈራ ነበር:: በዚያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ከነበረው ፍርሃት ይልቅ ለሰው የነበረው ፍርሃት ይልቅ ነበር ይሁንና ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅር እንከን የለሽ አልነበረም:: የነበረው ፍቅር እንከን የለሽ ቢሆን ኖሮ ለሰው የነበረውን ፍርሀት አስወግዶ እግዚአብሔርን አይክድም ነበር::

እግዚአብሔርን መፍራት በቅዱስ ጴጥሮስ ልብ ውስጥ በዚያን ሰዓት እንዲኖር እንመኛለን:: ሌሎቹ አይነት ሰዎች ፍቅርን በተሳሳተ መልኩ ይተረጉሙታል እግዚአብሔርን በርህራሄው ማሸነፍ እንደሚችሉ ያምናሉ ስለዚህ ይቅር ይላል ደግሞም አይቀጣም ይላሉ:: በዚህ መሰረት ፍርሀት የላቸውም ኃጢአትንም ይሰራሉ:: እንደዚህ አይነት ሰዎች የተሳሳቱ ናቸው:: እንዲህ ብለው ያስባሉ ምናልባትም በግልጽ የምናመል ከው አምላክ መልካም እስከ ሆነ ድረስ ፍርሃት ሊኖረን አይገባም ሁልጊዜም ይምረናልና ሊሉ ይችላሉ:: ጌታ አመንዝራዋን ሴት ይቅር ብሏል ከውስጧ ሰባት አጋንንት ያወጣላትን መግደላዊት ማርያምንም ይቅር ብሏል (ማርቆስ 16:9):: መልካሙ አምላካ ችን ቀራጩን ዘኬዎስን ተቀብሏል ደግሞ ቀራጩን ማቴዎስ ሐዋርያ እንዲሆን መርጦታል:: እሱ ሁልጊዜ ለኃጢያተኞች ርህሩህ ነው:: እንደዚህ አይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን

www.ethiopianorthodox.org

ፍቅር በተሳሳተ መልክ ይተረጉሙታል፡ ደግሞም ትዕዛዛቱን ይተላለፋሉ።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ስለመፍራት ማውራት በጣም ጥቅም አለው በተለይ በዚህ ትውልድ ውስጥ። ሰዎች ለእግዚአ ብሔር ያላቸው ፍርሀትን ባጡበት ዘመን ላይ በመኖር እንገኛ ለን አንዳንዶች እግዚአብሔርን ሲነቅፉ ሲከሱና በእግዚአብሔር ላይ ሲያጉረመርሙ ሌሎች ደግሞ መኖሩን ይክዳሉ። ያለምንም ፍርሀት በድፍረት ትዕዛዙን የሚተላለፉም አሉ። ሁሉም አይነት ፀያፍ ነገር በዚህ ትውልድ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። ብዙዎች በህጎቹ ላይ በማመጽ ትክክል ያልሆነውን ዳኛ መንገድ ይከተላሉ። ስለእርሱም እንዲህ ተብሏል «እግዚአ ብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበር» (ሉቃስ 18:2)

እግዚአብሔርን መፍራት ከብዙ ሰዎች ልብ በተወገደበት በዚህ ትውልድ መካከል እግዚአብሔርን ስለ መፍራት ማውራት አለብን። በአባቶች በእናቶች በአስተማሪዎች በአዛውንቶች ወይም በኃላፊዎች ውስጥ ምንም ፍርሀት የለም። ይልቁንም በቤት በስራ ወይም በትምህርት ቤት አለቆች ላይና በህጎችና በደንቦች ላይ ማመጽ ነው ያለው። እግዚአብሔርን መፍራት ከምን ጊዜውም በላይ በተመናመነበት ጊዜ ላይ እንገኛለን።

አንዳንዶች እግዚአብሔርን መፍራት የብሉይ ኪዳን ባህሪ ነው ብለው ሊቃወሙ ይችላሉ ነገር ግን አዲስ ኪዳን የፀጋ እና የፍቅር ኪዳን ነው። እግዚአብሔር ትላንትና ዛሬም ነገ እስከለዘላለም ያው ነውና ይህ የተሳሳተ ገንዛቤ ነው። (ዕብራውያን 13:8) በእርሱ ዘንድ መለወጥ ወይም በመዞር



የተደረገ ጥላ የለም። (ያዕቆብ 1:17) እግዚአብሔርን መፍራት ባለፈው ጊዜ ስለነበር አሁንም የፍቅር ትዕዛዝ አለ። «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ በፍፁምም ነፍስህና በፍፁምም ኃይልህ ውደድ» (ዘዳግም 6:5) ጌታ ኢየሱስ ህጉም ሁሉ እና ነቢያት በፍቅር ትዕዛዝ ተሰቅለዋል ብሏል። (ማቴዎስ 22:40)

አዲስ ኪዳን ስለዚህ ፍቅር ሲያረጋግጥ እግረመንገዱን እግዚአብሔርን ስለ መፍራትም ይናገራል። ጌታችን እንዲህ ብሏል «እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ ከገደለ በኋላ ወደ ገሀነም ለመጣል ስልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ እር ሱን ፍሩ። (ሉቃስ 12:4:5) በአንድ ትዕዛዝ ውስጥ ፍርሃት የሚለውን ቃል 3 ጊዜ ደጋግሞታል። ፍቅር እግዚአብሔርን መፍራትን አይቃወምምና እንዲህ በማለት ጀምሯል። «ለእናንተ ለወዳጆቼ እላችኋለሁ . . .»

ቅዱስ ጴጥሮስ ለሁሉም ሰው እንዲህ ብሏል «. . : በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ። 1ኛጴጥ. 1:17) ለሴቶች ደግሞ እንዲህ ብሏል . . . በፍርሃት ያለውን ንጹሁን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ . . . (1ኛ ጴጥ. 3:2)

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ፍርሃት ለስለስ ባለ መልኩ አልተናገረም። እስቲ ስለ ፍርሃት ያለውን እንስማ። «. . . በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ . . . » (ፊልጵ. 2:12) ስለዚህ ፍርሃት በሚለው ላይ መንቀጥቀጥ የሚለውንና የበለጠ ጠንከር የሚለውን ቃል ጨምሯል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለፍርሃት በጣም ግልጽ የሆነውና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ጥቅስ እንዲህ ይላል»... በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን . . . »

www.ethiopianorthodox.org

(2ኛቆሮ. 7:1) ይሁዳም «አንዶንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ አንዳንዶች ንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳን እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ::» ብሏል:: (ይሁዳ 1:22-23)

ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራትን ነፍሳችን እንደማዳኛ መንገድ መጠቀም ይችላል:: ለአንዳንዶች ርህራሄ ይኖረናል ሌሎችን ደግሞ ነገ ከእሳት ውስጥ ነጥቀን እናወጣቸዋለን:: ስለዚህ አይቃጠሉም:: ሁሉም ሰው አንድ አይነት አይደለም:: አንዳንዶች ከፍርሃት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ::

በዚህ አቅጣጫ ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስ እንዲህ ይላል «ሌሎች ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሰሩትን በሁሉ ፊት ገስጻቸው:: «(1ኛ ጢሞ 5:20) ሌሎች ሰዎች ነገሮችን በቀላሉ እንዳይመለከቱ ይህ ፍርሃት በጣም ጠቃሚ ነው::

ሐናንያና ሰጲራን ለመቅጣት እንዲህ አይነቱ የፍርሃት አቀራረብ ጠቃሚ ነበር:: በሐናኒያና ሰጲራ የተሰራው ስህተት በኋላ ሰዎችም ሊደግም ይችላል:: ነገር ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ሲቀጣቸው በሐዋርያት ስራ ላይ እንደተጻፈው ከፍተኛ ፍርሃት ሆነ:: «በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ::» (የሐዋ. ሥራ 5:11) ይህ ፍርሀት ለቤተ ክርስቲያን ጥሩና የተረጋጋ መሆን በጣም ጠቃሚ ነበር::

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የኖረችው እንዲህ ባለ አስተምህሮ ነው:: ታዲያ አንዳንዶች ለምንድነው በአዲሱና በብሉይ ኪዳን አስተምህሮ መካከል ለመለያየት የሚፈልጉት? መጽሐፍ ቅዱስ አንድ አይነት አይደለም? በሐዋርያት እንዲህ



ተብሎለታል «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል::» (2ኛጢሞ. 3:16)

በብሉይ ኪዳን የነበረው እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው:: እርሱ አይለወጥም ስለኃጢአት ስታስቡ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ጥብቅ እንደሆነ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለዘብተኛ እንደሆነ አታስቡ:: በእርሱ ከፍተኛ ጥላቻ ውስጥ ኃጢአት ተመሳሳይ ነውና እግዚአብሔር ይከለክላል:: ደግሞም እግዚአብሔር በቅድስናው ተመሳሳይ ነው ስለዚህ እርሱ በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ መልካም ቅዱስ እና ጻድቅ ነው::

ስለዚህ ብሉይ ኪዳን የፍርሃትና የቅጣት አዲስ ኪዳን ደግሞ የፍቅርና የፀጋ ኪዳኖች ናቸው ማለት አይደለም:: ፍርሃትና ደስታ በሁለቱም ኪዳኖች ውስጥ አሉ:: ለሚያምኑና በእምነት ለሚቆዩ ደስታ ለማያምኑና ከእውነት ለሚሸሹ ደግሞ ፍርሃት ይሆናል::

አዲስ ኪዳን ተስፋ የተሰጠበት ብሉይ ኪዳን ደግሞ የስጋትና የስቃይ ኪዳን አይደሉም:: «እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል» (ማቴ 3:10) ተብሎ በአዲስ ኪዳን ላይ ተጽፏልና ስጋትና ተስፋ በሁለቱም ኪዳናት ውስጥ አሉ::

ጌታችን በሙሉ ፍቅሩ እንዲህ ብሏል «በእኔ የማይኖር ቢኖር እንደቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሏቸዋል ያቃጥሉአቸውማል::» (ዮሐ. 15:6)

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር የሰውን ተፈጥሮ ያውቃል ደግሞም ፍርሃት ለተፈጥሮዋችን ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል:: ስለዚህ በአዲሱም ሆነ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለፍርሃት ይናገራል:: በብሉይ ኪዳን ሰዎችን ለማስፈራራት ብቻ በታሰበ መልኩ ሳይሆን በፍቅርና በጸጋ ስለ ፍርሃት ይናገር ነበር::

በመዝሙረ ዳዊት ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው ቃል ኪዳንኑም ያስታውቃቸዋል::» (መዝ. 25:14) «እነሆ የእግዚአብሔር አይኖች ወደ ሚፈሩት ናቸው::» «(33:18) «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰለፋል ያድናቸውማል::» (መዝ. 34:7) «ማዳኑ ለሚፈሩት ቅርብ ነው::» (መዝሙር 85:9) «. . . ምህረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ::» (መዝሙር 103:11) «. . . እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማነው? በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል:: ነፍሱ በመልካም ታድራለች ዘሩም ምድርን ይወርሳል::» (መዝሙር 25 :12)

በትንቢተ ኤርምያስ ላይም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «ለእነሱም ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ለዘላለም እንዲፈሩኝ አንድ ልብና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ:: ለእነርሱም ከማደርገው በጎነት አልመለስም ስል ከእነርሱ ጋር ለዘላለም ቃል ኪዳን እገባለሁ ከእኔም ዘንድ ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ::» (ኤር. 32:39:40)

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን አለመፍራት ከኃጢአት ጋር የተያያዘ ሲሆን እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ



ሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚፀልይ ነበር::» (ሐዋርያት ስራ 10:2)

ሽባው ሰው ሲፈወስ ያዩ ሰዎች ፍርሃትና እግዚአብሔርን ማክበር ተደባልቆባቸው ነበር:: «ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸው ታላቅ ነብይ በእኛ መካከል ተነስቶአል ደግሞ እግዚአብሔር ህዝቡን ጎበኘ እያሉ አመሰገኑ::» /ሉቃስ 7:16/

በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ላይ ቅዱስ ዮሐንስ አንድ ነገር አየ:: በምድርም ለመኖሩ ለህዝቡም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ በታላቅ ድምፅም የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡ ሰማይንና ምድርንም ባህርንም የውሐንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ::» (ራዕይ 14:6-7) በተጨማሪም እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ ሲያመልኩት አየ «. . . ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማነው? አንተ ብቻህን ቅዱስ ነህ. . .» (ራዕይ 15:4)

ይህ ቃል ቅዱስ ጴጥሮስ በመልዕክቱ ላይ ከጻፈው ጋር ተመሳሳይ ነው:: . . . «ወንድሞችን ውደዱ እግዚአብሔርን ፍሩ . . .» (1ኛጴጥ 2:17) እግዚአብሔርን መፍራት ከጥሩነት ጋር እንደሚጣመር ሁሉ እግዚአብሔርን አለመፍራት ደግሞ ከኃጢአት ጋር ይጣመራል:: ስለዚህ በመስቀል ላይ ኃጢአቱን የተናዘዘው ወንበዴ ሌላኛውን እንዲህ ብሎ ይነቅፈዋል «. . . አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? ስለአደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና . . .»

www.ethiopianorthodox.org

(ሉቃስ 23:40 41) ስለ ስህተተኛው ዳኛም እንዲህ ተብሏል «እግዚአብሔርን የማይፈራ . . .» (ሉቃስ 18:2)

የአባቶቻችን አባት አብርሃም በጌራራ ምድር በእንግድነት በተቀመጠበት ወቅት እንዲህ አለ «. . .በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን መፍራት በእውነት እንደሌለ ለሚስቴም ሲሉ እንደሚገድሉኝ ስላሰቡህ ነው::» (ዘፍጥረት 20:11) በማለት ተናግሯል::



## ምዕራፍ ሁለት

## የፍርሃት ምንጮች

የቅድስናን ዘውድ የሚጎትት መላእክት ፍርሃት የለባቸውም:: በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ሁልጊዜ ኃጢአትን ስለሚሰሩ ፍርሃት ሁልጊዜ ይከተላቸዋል ፍርሀት ኃጢአትን ይቀድማል ይከተለውማል ደግሞም በተከታታይ የተቆራኙ ናቸው::

### የመጀመሪያው አይነት ፍርሃት
### የመውደቅ ፍርሃት ነው

ይህ ፍርሃት ኃጢአትን የሚቀድም ነው:: ሰውን ጥንቁቅ ስለሚያደርግ በጣም ጠቃሚ ነው:: ንፁህ የሆነ ሕይወትን መምራት የሚፈልግ ሰው መውደቅን ይፈራል:: ስለሀጢአት እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «ወግታ የጣለቻቸው ብዙዎች ናቸውና እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው::» (ምሳሌ 7:26) በእርግጥም ኃጢአት እንደነ ዳዊት ሰሎሞንና ሶምሶንን የመሳሰሉ ታላላቆችን ከደቀመዝሙርነት ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ቶማስን ጥላለች:: ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በማስጠንቀቅ እንዲህ ያለው «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ::» (ሮሜ 11:20)

በተፋፋመው መንፈሳዊ ውጊያና በአታላይ የሰይጣን ኃይል ምክንያት ለመጠንቀቅ ያህል እያንዳንዱ መንፈሳዊ ሰው እንዳይወድቅ መፍራት አለበት:: ቅዱስ ጳውሎስ አታላይ ስለሆነው ሰይጣን እንዲህ ይላል «. . . ባላጋራችሁ ዲያብሎስ

www.ethiopianorthodox.org

የሚውጠውን ፈልጎ እደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና . . .» (1ጴጥ 5:8) ስለመንፈሳዊ ውጊያዎችም «መጋደላችን ከስጋና ከደም ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉ መንፈሳውያን ሰራዊት ጋር ነው እንጂ::» በማለት ሲገልጽ (ኤፌ. 6:12) በተጨማሪም «ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ::» (1ኛቆሮንቶስ 10:12) እኛን ለማስጠንቀቅ ደግሞ ስለራሱ እንዲህ ይላል «. . . ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ::» (1ኛ ቆሮንቶስ 9:27)

ምንም እንኳን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ቢሆንም ይህንን ያደርግ ነበር:: በዚህ ምክንያት ነው ቅዱስ ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን እንዲህ በማለት የወቀሰው «እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በስጋ ትፈጽማላችሁን?» (ገላ. 3:3) ስለዚህ እንዴት እንደ ጀመርንና አሁን እንዴት እንዳለን ማወቅ ሳይሆን የሚጠቅመው የሕይወታችን ፍጻሜ እንዴት እንደሚሆን ማወቅ ነው የሚጠቅመው::

ይህ ከኃጢአት ጋር የሚዛመደው የመጀመሪያው አይነት ፍርሀት ነው:: በኃጢአት ላይ የመውደቅ ፍርሀት ነው:: መዝሙረኛው ዳዊት የተናገረውን በማድመጥ መንፈሳዊ ሰዎች ከዚህ ማምለጥ ይችላሉ:: «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ::» (መዝ. 1:1)



አንድ ሰው ኃጢአትን ከሰራ በኋላ ፍርሃት ውስጥ ይወድቃል ይህ ደግሞ የመጋለጥ ፍርሃት ነው:: ኃጢአቱ ተጋልጦበት ውርደትና ሞገስ ማጣት ውስጥ እንዲሁም ዝናውን በሚያጠፉ የሰዎች ምህረት የለሽ ወሬ ውስጥ እንዳይወድቅ ይሰጋል::

ስለዚህ የስነልቦና ባለሙያዎች «ወንጀለኛ ወንጀል የፈጸመበት አካባቢ ምልክት ረስቶ እንዳይሆን በመፍራት ወንጀል የሰራበት አካባቢ ይመላለሳል» ይላሉ:: መርማሪዎች ይህንን የሥነ ልቦና ጫና ይጠቀማሉ:: ስለዚህ ምንም አይነት ምልክት ለወንጀለኛው ሲነግሩት በጣም ይጨነቃል::

የመጋለጥን ፍርሃት በተመለከተ ብዙ ጊዜ ኃጢአት የሚፈጸመው በድብቅና በጨለማ ውስጥ መሆኑን ማንሳቱ ጠቃሚ ነው:: «. . . ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ. . .» (ዮሐ. 3:19) ተብሎ ስለ ኃጢአተኞች ተጽፏል:: «ክፉን የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል::» (ዮሐ. 3:20-21)

ስለዚህ ቅዱሳን የብርሃን ልጆች ይባላሉ ክፉዎች ደግሞ ኃጢአታቸውን በጨለማ ውስጥ ይፈጽማሉና የጨለማ ልጆች ተብለው ይጠራሉ:: መጽሐፍት የሚከፈቱበትና ክፉ ሥራዎቻቸው የሚገለጥበትን ሀሳብና ዝንባሌዎቻቸው የሚፈተኑበትን የመጨረሻውን ቀን ይፈራሉ:: የመጨረሻውን ቀን እንዴት ሊያመልጡ ይችላሉ? የትስ ይደበቃሉ?

www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአታቸው በምድር ላይ በምንም አይነት ምክንያት ባይገለጥ እንኳን በጻድቁ ዳኛና በፍርድ ቀን በሚገኝ ሁሉ ፊት መገለጡ አይቀርም:: በምስጢራዊ ስፍራዎች የተነገሩን በሙሉ ይገለጥብናል ብለው ይፈራሉ:: ጌታችንም እራሱ በተናገራቸው በእነዚህ አስፈሪ ቃላት ሳይቀር ይፈራሉ:: «. . .የማይገለጥና የተከደነ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና::» (ማቴ. 10:26) ምንም ነገር በማይደበቅበት ነገር ግን ሁሉም በሚገለጥበት ጊዜ ፊታቸውን የት ሊደብቁ ይችላሉ?

መንፈሳዊ የሆነ ሰው ሊጨነቅበት የሚችል አንድ ሌላ ጉዳይ አለ:: ኃጢአቶቹ ይወዱት ወይም ያደንቁት በነበሩ በሞት ከዚህ ዓለም በተለይ ሙታን መንፈስ ፊት ይገለጥና ይገረማሉ ወይም ይነቅፉት የነበሩት ትክክል እንደነበር ይረዳሉ:: ስለዚህ አንድ ሰው ስለዚህ ምን ላድርግ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል::

ንስሀ ምንም እንዳላደረጋችሁ አድርጎ ኃጢአታችሁን ሊያጠፉ እንደሚችል ልነግራችሁ እችላለሁ:: አጥቦ ከበረዶ በላይ ያነጣችኋል:: ኃጢአቴ ይታወቅብኛል ብላችሁ ለተጨማሪ ጊዜ አትስጉም:: ኃጢአቴ ይገለጥብኛል ብላችሁ የምትፈሩ ከሆነ ተናዘዙና የእግዚአብሔር መልእክትና የቅዱሳን መንፈስ በእናንተ ደስ ይላቸዋል:: በአንድ ኃጢአተኛ ንስሐ በሰማያት ደስታ አለና:: (ሉቃስ 15:7)::



## የፍርድ ወይም የኃጢአትን መዘዝ መፍራት ከኃጢአት ጋር የተያያዘ ፍርሃት ነው

አባታችን አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ ፈራና በዛፎች መካከል ተሸሸገ:: ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የፍቅር ግንኙነትም ወደ ፍርሃት ግንኙት ተቀየረ:: ነፍሰ ገዳዩ ቃየንም ፈርቶ ብቻ ሳይሆን በጭንቀት ተሞልቶ ስለነበር እንዲህ አለ «. . . ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት:: እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ. . .» (ዘፍ. 4:13-14) መዝሙረኛው ዳዊት ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ፈርቶ ነበር እና እንዲህ አለ «አቤቱ በቁጣህ አትቅሰፈኝ በመዓትም አትገስፀኝ:: ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ::» (መዝ.ዳዊት 6:1-2)::

## ኃጢአተኛ ሁለት አይነት ቅጣቶችን ይፈራል ምድራዊና ሰማያዊ

ሰማያዊው ቅጣት አስቃቂና ዘላለማዊ ነው:: በመቀጠል በደንብ አድርጌ እንደማብራራው ተስፋ አደርጋለሁ:: ምድራዊው ቅጣት እራሱ ብዙ አይነት ነው:: ህብረተሰቡ ከጥላቻ የመነጨ አሉባልታ በማካሄድ በማግለልና ተአማኝነትን በማሳጣት ሊቀጣ ይችላል:: ቅጣቱ ህግን መሰረት ያደረገ እስራትና ከዚህም ጠንከር ያለ ነገር ሊሆንም ይችላል:: ወይም ደግሞ እግዚአብሔር በበሽታ አካልን በማጉደል ወይንም በዘዳግም ምዕራፍ 28 ላይ

www.ethiopianorthodox.org

ከተጠቀሱት መቅሰፍቶች በአንዱ ሊቀጣን ይችላል:: ልጃችንን ወይም ደግሞ የልጅ ልጆቻችንን በሚያጠቁ ቅጣትም ሊቀጣን ይችላል::

ጥንቁቅ ሰው የሚፈራቸውና ኃጢያተኛውን ሰው የሚከተሉ መንፈሳዊ ፍርሀቶች አሉ:: የእግዚአብሔር ቁጣ እና በቀልን ይፈራል:: እግዚአብሔር ንጉሥ ሳኦልን በ1ኛ ሳሙ ምዕራፍ 16 ቁ. 8 ሳይቀበለው እንደቀረው::

የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝን ይፈራል:: ከዚህ ባሻገር የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ እንዳይለይ ይፈራል (1ኛሳሙ. 17:14) ወይም የእግዚአብሔር ፀጋ ትቶት እንዳይሄድና እግዚአብሔር ለማይረባ አዕምሮ ወይም ለልቡ ፍትወት አሳልፎ እንዳይሰጠው ይፈራል:: (ሮሜ 1.24 – 28) አዲስ ሆኖ የተፈጠረበትን መለኮታዊ መልክ እንዳያጣም ይፈራል:: ዘውዱን እንዳያጣና መቅረዙ ከስፍራው እንዳይወሰድበት ይሰጋል:: (ራዕይ 2:5) በሰይጣን ቁጥጥር ስር ወድቆ ፈቃዱንና የእግአብሔርን ልጅ ነፃነት በማጣት ክፉን ነገር እንዳይፈጽም ይሰጋል::

ስለዚህ ወደ ክፉ ሁኔታ ውስጥ እንዳይገባ ይፈራል:: ጌታ እንዲህ እያለ ሲናገር መስማትም ይፈራል:: «ስራህን አውቃለሁ ሕያው እንደመሆንህ ስም አለህ ሞተሀል::» (ዮሐንስ ራዕይ 3:1) እግዚአብሔርን ለመገናኘት ዝግጁ ባልሆነበት ሰዓት ሞት በድንገት እንዳይወስደውም ይፈራል::

በአንድ ወቅት አንድ ሰው እንዲህ አለ (ሦስት ነገሮችን እፈራለሁ ነፍሴ ከስጋዬ የምትለይበትን ጊዜ ከጻድቁ ዳኛ ፊት የምቆምበትን ጊዜ እና የእርሱን ፍርድ የምሰማበትን ጊዜ::) ከፍተኛ ንፅህናን የተላበሱ ቅዱሳን እንዲህ ከፈሩ እኛስ?



እግዚአብሔርን የሚፈራ ኃጢአትን አይሰራም ኃጢአትን የሚሰራ ደግሞ እግዚአብሔርን አይፈራም::

እግዚአብሔር በአስጨናቂዎች ላይ እንደሚፈርድ ያውቃልና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሌሎችን አያስጨንቅም:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ያውቃልና ወደ ጥፋት አይገባም:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እግዚአብሔር እንደሚያይና እንደሚሰማ የልባችን ጥልቀት ድረስ ዘልቆ ሁሉን እንደሚያውቅ ያውቃልና በድብቅም ቢሆን እንኳን ክፉን አይፈጽምም::

ኃጢአትን ሠርተው ምንም ስለማይፈሩ ሰዎች ምን ታስባላችሁ ብሎ አንድ ሰው ሊጠይቅ ይችላል:: እንዲህ አይነቱ ሰው ወደ ግድ የለሽነትና ስርዓት አልበኝነት ውስጥ ገብቷል እንላለን:: ወይም ደግሞ ህሊናው ታሟል ወይም አይሰራም ወይም እራሱን ቆም ብሎ እንዳይመረምር በዓለም ግርግር ተወስዷል:: በመንፈሳዊ የህሊና መሳት ውስጥ ነው ያለው ቢያገግም እንኳን በእርግጠኝነት ይጎዳል:: እንደዚህ አይነት ሰዎች ወደሞት በቀረቡ ቁጥር ለመጨረሻው ጊዜ ስላልተዘጋጁ ይፈራሉ እና ደግሞ ሕይወታቸውን በከንቱ እንዳሳለፉ ያስባሉ::

እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ:: «የፍርሃትን ሳይሆን የፍቅርን ሕይወት መምራት እፈልጋለሁ» እንዲህ እላችኋላሁ «ኃጢአት ከፍርሃት ጋር የተዛመደ ነውና ኃጢአትን አትሥሩ»::

ኃጢአተኛው ኃጢአትን በሚሠራበት ጊዜ እግዚአብሔርን የመፍራት ነገር የለበትም ወይም መዝሙረኛው እንዳለው እግዚአብሔርን ከፊቱ አላስቀመጠም:: ኃጢአት የሌለብህ ከሆንክ አትፍራ:: ኃጢአትን ከሠራህ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር

www.ethiopianorthodox.org

ከታረቅክ እራስህን ውቀስና የንስሀ ኑሮ ኑር። ከዚህ በኋላ ፍርሃት አይኖርብህም።

ነገር ግን ኃጢአተኛ እስከሆንን ድረስ ጌታችን እራሳችንን ማረም የምንችልበትን ፍርሃት ሰጥቶናል። ሐዋርያው እንዲህ ሲል ስሙት «እንግዲህ ወደ እረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።» (ዕብ. 4:1) ፍርሃት ከኃጢአት ያስጥ ላልና የመጨረሻውን ቀን እንዳትፈሩ ከፈለጋችሁ አሁን ፍሩ። ከመጨረሻውም ቀን ፍርሃት ትነጻላችሁ።



## ምዕራፍ ሦስት

# እግዚአብሔርን የመፍራት ጥቅሞች

**1** እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ንስሀና በትዕዛዙ ውስጥ ወደ መኖር ይመራል።

እግዚአብሔርን መፍራት ኃጢአትን ከመስራት ይጠብቀናል። ነገር ግን ኃጢአትን ብንሰራ እግዚአብሔርን መፍራት የኃጢአትን መዘዝና የእግዚአብሔርን ቅጣት እንዳንፈራ ያደርገናል። ይህ ደግሞ ወደ ንስሀና ትዕዛዙን ወደ ማክበር ይወስደናል። ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ከኃጢአት ይጠብቀናል። ኃጢአትን ከሰራን ደግሞ ወደ ንስሀ ይመራናል።

**2** እግዚአብሔርን መፍራት የመንገዱ መጀመሪያና መንፈሳዊ ምሽግ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከመንገድ ላይወጣ ይችላል።

በመንገዳችን እግዚአብሔርን ከፊት አድርገን ከጻድቁ ዮሴፍ ጋር እንዲህ እንላለን «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሰራለሁ?» (ዘፍጥረት 39:9) «የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው።» (ሮሜ 6:23) ተብሎ የተቀመጠውን ቃል በመፍራት እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ኃጢአትን አይሰራም። በራእይ 3:1-15 ላይ «ሥራህን አውቃለሁ» ብሎ ያለውን ሁሉን የሚያውቀውን እግዚአብሔርን ይፈራል። ከዚህም በላይ የእግዚ

www.ethiopianorthodox.org

አብሔርን ማስጠንቀቂያና ቅጣት ይፈራልና ኃጢአትን ከማድረግ በመቆጠብ ትዕዛዝን ይፈጽማል:: በልቡ ውስጥ ያለው እግዚአ ብሔርን መፍራት ደግሞ በኃጢአት እንዳይወድቅ ምሽግ ይሆነዋል::

**3 እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ይታዘዘዋል እግዚአ ብሔርን የማይታዘዝ ሰው ግን እግዚአብሔርን እንደ ማይፈራ ይመሰክራል::**

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሁሉንም ነገር ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያደርጋል:: ጌታችን በትንቢተ ኤርሚያስ መጽሐፍ ላይ እንዲህ ይላል:: «. . . እነርሱም ህዝብ ይሆንኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ:: ለእነርሱም ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ለዘላለም እንዲፈሩኝ አንድ ልብና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ::» (ኤር. 32:38-40)

**4 እግዚአብሔርን መፍራት አንድን ሰው ጥንቁቅ እንዲሆን ያስተምረዋል::**

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ወድቆ የእግዚአብሔርን ስሜት እንዳይጎዳ ይፈራልና:: የሚያደርገውንና ሊያደርግ የሚ ያስበውን ነገር በጥንቃቄ ይፈጽማል:: «ስለዚህ የቆመ የሚመ ስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ::» (1ኛቆሮ 10:12) በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ሊያነቃቃን ይፈልጋል:: እንዲህም ደግሞ ይላል:: «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ::» (ሮሜ 11:20)



እመኑኝ እንደውም አንዳንዶች ስነልቦናዊ መበሳጨት እግዚአብሔርን መፍራት በሚለው ነገር የተነሳ ሊይዛቸው ይችላል ነገር ግን ጥንቁቅ በሆኑ ቁጥር መንፈሳዊ ጥቅም ያገኛ ሉ:: እየወደቁ እንዳይሆን በመፍራት ድንጋይ ባደናቀፋቸው ቁጥር በጥልቀት ያስባሉ:: ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራት በልባቸው ውስጥ ምንም ሥፍራ ከሌለው «ምንም ማትጨነቅ ከሆነ የምትደፍረውን በሙሉ አድርግ::» የሚለውን አባባል መተግበር ይጀምራሉ::

**5 እግዚአብሔርን መፍራት ከሚተውት ብዙዎች ዋጋ የለሾች እና የረከሱ ይሆናሉ::**

እንዲህ ሊሉ ይችላሉ እስቲ በፍቅር እንኑር፤ ፍቅር ጥንቁቅ መሆንን ይከለክላልን? እግዚአብሔር መፍራት ከሚተ ውት መካከል ብዙዎቹ ኩሩና ልባቸው የደነደነ ይሆኑና አለን ብለው የሚያውጅትን ፍቅር ያጡታል::

**6 እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ከእግዚአብሔር ሲገናኝ በትህትና ነው የሚገናኘው**

እግዚአብሔርን ሳይፈሩ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እንደሚኖሩ የሚናገሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኙ የሚያወሩት ትክክለኛው ስርአት (ባህሪይ) ባልጠበቀ መልኩ ነው:: መቀራረብን ምክንያት በማድረግ ኃጢአትን እግዚአብሔርን ሳይፈሩ ይፈጽማሉ::

www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳን አባታችን አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ቢሆንም ለሰዶምና ገሞራ ሲማልድ ግን እንዲህ አለ «. . . እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ . . .» (ዘፍ. 18 :27) በትንቢተ ሚልክያስ ላይ እግዚአብሔር እንዲህ አለ «ልጅ አባቱን ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንኩ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንኩ መፈራቴስ ወዴት አለ? (ሚል. 1:6)

## 7 እግዚአብሔርን መፍራት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ትጉህ ወደ መሆን ይመራል::

ፍቅርን ለማመካኘት አንዳንድ ሰዎች ምንም እገዳ የለባቸውም:: ሕይወታቸው ግድየለሽነትና ትጋት ማጣትን የተሞላ ነው:: በፍፁም ጥንቃቄ አይደሉም ስለምንም ነገር ግድ የላቸውም እና ምንም ነገር አይፈጽሙም:: የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ችክ ብሎ መፈጸም እንደፈሪሳውያን መሆን እንደሆነ ያስባሉ:: ከህግ በታች አይደለንም ይላሉ:: ስለዚህ ግድ የለሽ ወደመሆን ይደርሳሉ::

በሌላ በኩል እግዚአብሔርን የሚፈራ መንፈሳዊ ሰው ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ነው:: እግዚአብሔር መፍራትን ጠብቆ መኖር በአይኑ ፊት ነውና እግዚአብሔር በሰጠው ጥቂት ነገር ላይ ታማኝና ትጉህ ነው::

እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰው እራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠም ትጉህም አይደለም:: በሚያሳዝን መልኩ እንዲህ አይነት ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እናገኛቸዋለን:: አንድ



አገልጋይ በጣም ወሳኝ በሆኑ የወጣቶች ስብሰባ ላይ ተጋብዞ ለመምጣት ቃል ከገባ በኋላ አርፍዶ ሊመጣና ይቅርታ ሊጠይቅ ይችላል:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ግን በስብሰባው ላይ ችላ ስላላቸው ስለ እያንዳንዱ ሰው ይጠይቀኛል ብሎ ስለሚፈራ ቀጠሮዎችን ያከብራል:: በአይኖቹ ፊት እግዚአብሔርን መፍራት አለና በአገልግሎቱ ጥንቃቄና የተሰጠ ሆኖ ታገኙታላችሁ::

## 8 እግዚአብሔርን መፍራት በፀፀት ወደተሞላ ልብና ወደ ማዋረድ ይመራል::

እራስን በማዋረድ አንድ ሰው እንዲህ ይላል «እግዚአብሔርን ልቃወምና ትዕዛዙን ልጥስ እኔ ማነኝ?» ለመፀለይ ሲቆም እንዲህ ይላል» በእግዚአብሔር ፊት ልቆምና እርሱን ላነጋግር እኔ ማን ነኝ?» ጥሩው ምሳሌ ቀራጩ ፈሪሳዊ ነው::

ቀራጩ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ «ለእኔ ለኃጢአተኛው እራራልኝ» እያለ ደረቱን ይደልቃል እንጂ አይኖቹን ወደ መንግስተ ሰማይ አያነሳም:: እግዚአብሔርን በመፍራት ቆሟልና ይህ ፍርሃት በፀፀት ወደተሞላ ልብ ይመራዋል:: እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት ፈሪሳዊ ግን በጾሙና በአስራቱ ቀራጩን ይኮንን ነበር:: ከአመንዝሮች ከአመፀኞችና ከቀማኞች የተሻለ እንዲሆንም ይናገር ነበር:: (ሊቃስ 12:10-14)

www.ethiopianorthodox.org

**9** **እግዚአብሔርን አለመፍራት መሸነፍን ይወልዳል መሸነፍ ደግሞ እንባን ይወልዳል::**

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በጸሎቱና በአምልኮው ውስጥ የተሸነፈ ነው:: በፀፀት በተሞላ ልብ እያነባ ሊያለቅስ ይችላል:: እንዲህ አይነቱ ባህሪ ምንም እንኳን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ቢገኙም የቅዱሳን አባቶችን ባህሪ ነበር:: እግዚአብሔርን መፍራት በፀፀት የተሞላ ልብ መማረክና እንባ ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ቢደርሱም እስከሞታቸው ድረስ ተለይቷቸው አያውቅም::

ፍቅርን አግኝቻለሁ ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር በጠበቀ ህብረት እኖራለሁ ብሎ የሚያውጅ ሰው የሚፀፀትን ልብ ሲያጣና ማስተዋል የሌለው ሊሆን ይችላልና:: ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ግንኙነት ግድየለሽ ይሆናል:: ከዚህ በኋላ ኃጢአትን እንደውሀ ይጠጣታል:: እግዚአብሔር መሀሪና ሩህሩህ አምላክ ነው እያለ ወድቀቱን ለመሸፈንም ይሞክራል:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ግን አይኖቹ በእንባ ልቡ ደግሞ በፀፀት እስኪሞላ ድረስ ኃጢአቱ በፊቱ ነው::

**10** **እግዚአብሔርን በመፍራት የሚኖር ሰው ሁልጊዜ እራሱን ይፈትሻል::**

ስራውን ብቻ ሳይሆን ሀሳቡንና ፍላጎቱን ጭምር ይመረምራል:: ትልቅም ይሁን ትንሽ ለእያንዳንዱ ስራው እራሱን ይፈትሻል ስሜቱን ፍላጎቱን ሀሳቡን እና የምላሱንና የየስሜቱን ኃጢአት በሚቀዳ መሳሪያ ፊት እየደቆመ ያስባል:: ስለእያንዳንዱ የሕይወታችን ነገር ተጠያቂ ነንና በእርግጥም ይህ ነገር ትክክል ነው:: ስለእግዚአብሔር የተቀዳው ነገር ምን አይነት ነገር ቢሆን በፍርድ ቀን በመላእክትና በሰዎች ሁሉ ፊት ይገለጣል::

አመጻቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁአን ናቸው ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው:: (ሮሜ. 4:7-8) (መዝ. 32:1-2) ይላልና ይህንን ኃጢአታችሁ ከፈራችሁና ኃጢአታችሁን ከተናዘዛችሁ ኃጢአታችሁ ከመቅጃው ማሽን ላይ እንደሚደመሰስና ከዚህ በኋላ ተጠያቂ እንደማትሆኑ እርግጠኛ ሁኑ::

**11** **እግዚአብሔርን መፍራት በራስ ላይ ወደመፍረድ ብቻ ሳይሆን እራስን ወደመውቀስ ወደ ፀፀትና ንስሀም ይመራል::**

እግዚአብሔርን የሚፈራው ቅዱስ መቃርዮስ «ወንድሜ ሆይ በአንተ ላይ ከመፍረዳቸው በፊት በእራስህ ላይ ፍረድ» ብሎ የተናገረውን ይሰማል ከዚህ በመቀጠል በቀደመው ጊዜ ለሰራውና ሊያደርግ ስላሰበው ነገር ሁሉ እራሱን ይወቅስና ክፉውን ሀሳብ ያስወግዳል:: እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ንፁህ ልብ ይመራል::

www.ethiopianorthodox.org

## 12 እግዚአብሔርን ያስደስት ዘንድ እግዚአብሔርን መፍራት ሰውን ወደ ንቁነትና ትጋት ይመራል::

ለምሳሌ በጣም ብዙ ሊከታተለው የሚገባ ትምህርት ያለበት አንድ የኮሌጅ ተማሪ 1000 ገጽ የሚሆን የሚጠና ነገር ቢኖረውና እርሱ ግን ሀያውን ገጽ እንኳ ያላጠና ቢሆን ያሰበውን ነገር ለማሳካት ጥረቱን በእጥፍ እንዲጨምር በሚያደርገው ፍርሃት ይያዛል::

ለእኛ መንፈሳዊ ትምህርታችን ቅድስና ነው::«. . . እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ . . .» (1ኛጴጥ. 1:16) ያለውን እግዚአብሔርን ያለቅድስና ማየት አንችልም:: «እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተ ፍፁማን ሁኑ::» (ማቴ. 5:48) ብሏልና::

በእኛና በቅድስና እንዲሁም በፍፁምነት መካከል ረጅም ርቀት እንደመኖሩ መጠን በፍርሃት መኖር የለብንም? ምናልባት በድንገት ሲመጣ ተኝተን እንዳያገኘን (ማር. 13:36) ይህ ፍርሃት ወደ ትጉህነትና ንቁነት ለነፍሳችንም መዳን ወደመጠንቀቅ ሊመራ አይገባምን?» በተበሳጨን ቁጣርና ይህ ፍፁምነት የበቃ መስሎ በታየን ቁጥር የቅዱስ ጳውሎስን ምክር መስማት አለብን:: «እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ:: የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል::. . .» (1ኛቆሮ. 9:24-25) ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ያለመቆምና በትጋት ሁልጊዜ በመንፈሳዊው መንገድ ላይ ይገኛል::



## 13 እግዚአብሔርን መፍራት ወደ መንፈሳዊ እድገት ይመራል::

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው የፍፁምነት መንገድን ረጅም እደሆነ ስለሚያስተውልና ከመድረሱ በፊት እሞታለሁ ብሎ ስለሚፈራ በየቀኑ የተወሰነ መሻሻል ያሳያል:: እግዚአ ብሔርን የማይፈራ ሰው ወደታች በሚያፈገፍግበትና የባሰ በሚበላሽበት ወቅት እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ግን ለማደግ ይተጋል::

## 14 እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለእራሱ ብቻ ሳይሆን ስሌሎችም ይጨነቃል ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግ ሥት ለማወጅ ይጥራል::

ኢዮብ ስለልጆቹ ይጨነቅና ስለ እርሱ መስዋዕት ያቀርብ እንደነበር ሁሉ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ስለራሱና ስለ ሚያውቃቸው ሰዎች ዘላለማዊነት ይጨነቃል:: (ኢዩብ 1:5) ቅዱስ ጳውሎስ «በስጋ ዘመዶቼ ስለሆኑ ስለ ወንድሜቼ ከክር ስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንዳልሆን እጸልይ ነበርና::» (ሮሜ 9:23) ብሎ እንዳለ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በአ ገልግሎቱ ለሌሎች ደህና መሆን ይተጋል:: ለእግዚአብሔር መንግስት ያለው ፍቅርና አግልግሎትም ያድጋል::

www.ethiopianorthodox.org

**15** እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ጸሎት ይመራል።

ሰው ይታገላል ነገር ግን የእርሱ መታገል ብቻ በቂ ሳይሆን ሊቀር ይችላል። ስለዚህ ለእርሱና ለሌሎች የእግዚአብሔርን ፀጋና እርዳታ በመጠየቅ በፀሎት ይተጋል። እግዚአብሔር «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም. . .» (ዮሐ. 15:5) ስላለ የሰው ትጋት ብቻውን ለነፍስ መዳን በቂ አይደለም። ቅዱስ ጴጥሮስ በውሀ ላይ መራመድ ላይ ሳለ እሰጥማለሁ ብሎ ፈርቶ ወደ ጌታ ሲጮህ ጌታ እጆቹን ዘርግቶ እንደታደገው ሁሉ እግዚአብሔርን መፍራትም ወደ እግዚአብሔር መጠጋት ይመራል። (ማቴ. 14:30-31) ፍርሀት ሰውን ወደ ጠንቃቃነት ይመራል። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ «ጌታ ሆይ እርዳኝ ስለዚህ እድናለሁ» ይላል።

**16** እግዚአብሔርን መፍራት ወደ እውቀትም ይመራል ስለዚህ ግድየለሽነት ላይ አትወድቅም። ይሄ በተራው ትዕዛዝን ወደማንበብና መፈለግ ይመራል።

ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ በቀንም በማታም ፈቀቅ አትሉም ስለዚህ ከትዕዛዙ ትጠቀሙ ይሆናል። «በራስህም ማስተዋል አትደገፍ (ምሳሌ 3:5) ተብሎ ስለተጻፈ ግልጽ እንዲሆንላችሁ የምትፈልጉት ነገር ሲኖር የመንፈሳዊ አባቶቻችሁን ምክር ትፈልጉ ይሆናል።



**17** እግዚአብሔርን መፍራት ከሌሎች ጋር ወደመልካም ግንኙነት ይመራል።

«ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሀነም እሳት ፍርድ ይገባዋል።» (ማቴ. 5:22) የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ትፈራላችሁ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈርድባችኋል የሚለውን ስለሚያውቅ የሌሎችን ስሜት አይጎዳም፤ በሌሎች ላይም አይፈርድም። ጌታችን የሚ ምሩ ይማራሉና (ማቴ. 5:7) እንዳለ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ሁሉንም ሰው መሐሪ ነው ስለዚህ ምህረት ያገኛል።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ስራት

# እግዚአብሔርን መፍራት በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ

የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ስንል ቤተ ክርስቲያን እግዚአ ብሔርን በመፍራትና አማኞች እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በቅድ ስና ለመኖር በጣም ይጠነቀቁ የነበረበትን የሐዋርያት ዘመንና የመጀመሪያዎቹን የክርስትና ክፍለ ዘመናት ማለታችን ነው:: መለኮታዊ ትዕዛዞችን በመጠበቅ በኩል ቤተ ክርስቲያን በጣም ጥብቅ ነበረች:: ስለዚህ ስለክርስቲያን አማኞች እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ ኃጢአተኞችን ከባድ ቅጣት በመቅጣት ትታወቅ ነበር::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . .መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለስጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው::» (1ኛቆሮ. 5:5)፤ በማለት በቆሮንቶስ ኃጢአተኛ ላይ የተጣለውን ቅጣት እንረሳም:: ሐዋርያው ጳው ሎስ ኤልማስን እንዴት አድርጎ በዕውርነት እንደቀጣውም እና ስታውሳለን:: (ሐዋ.ሥራ 13:11)፤ ለደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎ ስም «ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሰሩት በሁሉ ፊት ገስጻቸው::» (1ኛጢሞ. 5:20) ብሎታል::

ይህ ፍርሀት ሌሎችን ስህተት ከመስራት ይጠብቃቸ ዋል:: በቀደሞዋም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአናኒያን የሰጲራ ታሪክ የማይረሳ ነው:: ለቅዱስ ጴጥሮስ በዋሹ ጊዜ ምንም



የንስሀ እድል ሳይሰጣቸው ቅዱስ ጴጥሮስ በሞት ቀጣቸው:: በሐዋርያት ስራ ላይ «በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህን በሰሙ ሁሉ ላይ ትልቅ ፍርሀት ሆነ::» (የሐዋ ሥራ 5:11) ተብሎ ተፅፏል:: ብዙዎችን ኃጢአትን ከመሥራት አግዷልና ይህ ፍርሃት ጠቃሚ ነበር::

ኃጢአተኛው ከአማኞች ጋር እንዳይገናኝ ማድረግ ከታላ ላቅ ቅጣት መካከል አንዱ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላይ «ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት::» (1ኛቆሮ. 5:13) ብሏል:: ካህናትን ከክህነታቸው እስከማውረድ የሚደርስ ሌላ አይነት ቅጣት ነበር:: አንዳንዶች እግዚአብሔርን ከመፍራታቸው የተነሳ በህብረተሰቡ ፊት ኃጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር::

በምድር ላይ እንዳሉት አስተዳዳሪዎች እግዚአብሔር ኃጢአትንና ክፉን ነገር አይታገስም:: (1ኛቆሮ 4:1 እና ቲቶ 1:7) ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን የተሞላችና ቅዱሳን ብቻ የሚገቡባት ነበረች::

መዝሙረኛው ዳዊት «. . . አቤቱ እስከረጅም ዘመን ድረስ ለቤትህ ቅድስና ይገባል:: (መዝ. 92:5)፤ እንዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ለሁሉም ሰው የተፈቀደ አልነበረም:: ስለዚህ ኃጢአተኞች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡት ሰዎች እንዲጸለይላቸው ለመለመን ስለነበር ለረጅም ዘመናት ቤተ ክር ስቲያን ኃጢአተኞችን በማግለል ቆይታለች::

የቤተ ክርስቲያን ቅጣት እጅግ በጣም ከባድ ስለነበር ሰዎች በጥንቃቄና በቅድስና እንዲኖሩ ያደረጋል:: ዲያቆናት ወይም ረዳት ዲያቆናት የቤተ ክርስቲያንን መግቢያዎች ይጠብቁ ነበር:: አለበለዚያ ግን ውሾች ወይም ድመቶች ይገባሉ::

www.ethiopianorthodox.org

የተከለከሉ ኃጢአተኞችም እንዳይገቡም ይጠብቃሉ። ቤተ ክርስቲያን የኃጢአተኛውን ሥልጣን ባላገናዘበ መልኩ ሁሉንም ኃጢአተኛ ትቀጣ ስለነበር ምንም ወገናዊነት አልነበረባትም።

## የታዋቂ ኃጢአተኛ ታሪክ

ሀብታሞችን ጓደኞቿ ያደረገች አንድ ታዋቂ ደናሽ ነበረች። አንድ ቀን ከነውድ ልብሶችና ጌጣጌጦቿ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደች። «ኃጢአተኛ ነሽና ወደ ቤተ ክርስቲያን የመግባት መብት የለሽም» በማለት ዲያቆኑ እንዳትገባ ከለከላት። እንደቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አንቺን መከልከል ሥራዬ ነው ደግሞም «. . .ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።» (1ኛቆሮ 5:13) ተብሎ ተጽፏል አላት። ሴቲቷ ከፍ ባለ ድምጽ ከእርሱ ጋር መከራከር ቀጠለች። ቄሱ ድምፁን ሰምተው ነገሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ወጡ» «አባቴ ሆይ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መግባት እፈልጋለሁ» በማለት ለቄሱ ነገረቻቸው። «ኃጢአተኛ ነሽና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መግባት አይገባሽም» ብለው ነገሩአት። ሁለተኛ ኃጢአት አልሠራም አለች። «የምትይው ትክክል ከሆነ ሂጂና ያለሽን ንብረት በሙሉ አምጪ» አሏት ቄሱ። ልብሶቿን ጌጣጌጦቿንና ያላትን ነገር በሙሉ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ይዛ መጣች። ከዘማዊ ምንም ነገር እንዳይቀበሉ የቤተ ክርስቲያን ህግ ያግዳልና ያመጣችው በሙሉ እንዲቃጠል አዘዙ። ይህንን ስትመለከት «ይህ ሁሉ በምድር ላይ ከተደረገብኝ ከሰማይስ?» አለች። በጣም የተሸነፈች ሆነች ወደ ቤተ ክርስቲያንም እንድትገባ ተፈቀደላት። እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ልቧ ውስጥ ገባና ንስሐ ገባች። በኋላ ላይ ቅድስናን አገኘች።



## የእግዚአብሔር ቤት ቅዱስነት

በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የደከሙትን አስወጥተው ለአማኞች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ዲያቆኑ «ምንም አይነት መናፍቅና አማኝ ያልሆነ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲቆይ አይፈቀድለትም።» ይል ነበር። እደዚህ አይነት ሰዎች ለቀው መውጣት አለባቸው። በቅዱስ ቁርባን ላይ የሚሳተፉ ቅዱሳን አማኞች ብቻ እንዲቆዩ ይፈቅድላቸውና በሩ ይቆለፋል። ምክንያቱም የረከሱት እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ምንም አይነት አርፍዶ የመጣ ሰው እንዲገባ አይፈቀድም። በተቀደሰውም ሰዓት ማንም እንዲወጣ አይፈቀድለትም።

ቤተ ክርስቲያን በጣም ጥብቅ በሆኑ ህጎች የተሞላች ስለነበረች በቅዱሳን አማኞች የተሞላች ነበረች። አሁን ግን በበደልና በክፋት የተሞሉ ጨካኝ የሆኑ ሰዎች ወደቤተ ክርስቲያን እንዲገቡና ስህተተኞች ቦታ እንዲይዙ በጣም ፈቃደኛ እየሆነች ነው። አንዳዶች እርስ በርሳቸው ይነቃቀፋሉ ይተቻቻሉ። ደግሞም ለእግዚአብሔር ቤት ቅድስና ጋር የማይስማማ ነገር ይፈጽማሉ።

የአባቶቻችን አባት ያዕቆብ ቤቴልን በመሰረተ ጊዜ እግዚአብሔር ለእርሱ ተገለጠለትና ያዕቆብ «. . . ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው።» (ዘፍ. 28:17) ብሎ ተናገረ። የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአተኞች ላይ በታወጀበት ጊዜም አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ ቅዱሳን ብቻ እንዲገቡ ለማድረግ ይህንን ጥቅስ ይጽፉታል።

www.ethiopianorthodox.org

## ሴሎች የቤተ ክርስቲያን እርምጃዎች

ልክ ዘካርያስ በድሆች ላይ የነበረውን ጭቆና እንዳነሳ ሁሉ እግዚአብሔርን በመፍራት በምትታወቀው በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ቄሶቹ ለማንም ሰው በትክክል ሰውየው ንስሀ እንዲገባና የኃጢአቱን መዘዝ ማስተካከሉን እርግጠኛ እስ ካልሆኑ ድረስ በቀላሉ ሥርዓትን አያደርጉም ነበር:: በኃጢአቱ የተፀፀተ ሰው ኃጢአቱ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ይሰማው ዘንድ የቤተ ክርስቲያንን ከባድ ቅጣት ይቀበል ነበር::

ቤተ ክርስቲያን ምንጩ ተገቢ እስካልሆነ ድረስ ምንም አይነት ስጦታ ሳትቀበል እንደኖረች ታሪክ ያስረዳናል:: መዝሙረኛው ዳዊት «የኃጢአተኛው ዘይት እራሴን አይቀባም» ብሏል:: መጽሐፍ ቅዱስም «ስለ ተሳልኸው ስእለት ሁሉ የጋለሞታይቱን ዋጋና የውሻውን ዋጋ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት አታቅርብ . . .» (ዘዳ. 23:18) በማለት ያስተምረናል::

በሐዋርያት ህግም ቤተ ክርስቲያን ምንጫቸው ትክክል አይ ደለም ያለችውን ምንም ዓይነት ስጦታዎች አትቀበልም ነበር::

እግዚአብሔርን መፍራት የግል ኃጢአትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ከመናፍቃንም ጋር የተያያዘ ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን::» (ገላ. 1:8) ብሏል:: የተረገመ ማለት የተወገዘ ማለት ነው:: የተወደደው ቅዱስ ዮሐንስ «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና::» (2ኛዮሐ. 1:10-11) ብሏል::

በዚህ መልኩ እግዚአብሔርን በመፍራት ቤተ ክርስቲያን ምንም አይነት የሀሰት ትምህርት አትቀበልም ነበር:: በአስተምህሮዋም በጣም ጠንቃቃ ነበረች:: የሀሰት ትምህርት የሚያስተምርን ሰው ቤተ ክርስቲያን በጣም ከመቅጣቷም በላይ እንደዚህ አይነት የሀሰት ትምህርቶችን ደረጃቸው ምንም ይሁን ምን ለመከላከል እና ለማውገዝ የክርስቲያን ኮሚቴዎች ይቋቋሙ ነበር::

እግዚአብሔርን ስለመፍራት ከቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንውሰድ:: ይሄ ፍርሃት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸው ጥንቁቅና ትጉህ በጥቂቱም ሆነ በብዙው ላይ ደግሞ ታማኝ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: በዚህ መልኩ እምነቱን እንደተቀበሉት በንፅህና በመጠበቅ ለእኛ ሰጥተውናል:: (2ኛ ጢሞቴዎስ 2:2)::

ውድ አንባቢያን ሆይ እስከአሁን እግዚአብሔርን ስለ መፍራት ይህን መግቢያ ጽፌላችኋለሁ አሁን ደግሞ «እግዚአብሔርን መፍራት ልናገኝ እንችላለን?» ወደሚለው ተግባራዊ ነጥብ እንሂድ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አምስት

### እግዚአብሔርን መፍራት እንዴት ማግኘት ይቻላል?

**(1) ኃጢአትን በጣም በመጥላትና መዘዝን በማወቅ እግዚአብሔርን መፍራትን ማግኘት ይቻላል::**

እግዚአብሔርን መፍራትን ለማግኘት ኃጢአትን ስንፈፅም ሁኔታችን ምን እንደሆነ መገንዘብ አለብን:: ኃጢአት ከእግዚአብሔር ከመላእክት ከቅዱሳንና ከማንኛውም መንፈሳዊ ነገር ይለየናል:: ፃድቅ ሰው እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ እርሱም ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚኖር ነው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው መንፈስ ቅዱስም በውስጡ ይኖራል:: (1ቆሮ. 3:16) በሌላ በኩል ኃጢአተኛ ኃጢአትን ሲሰራ የእግዚአብሔር ልብ ያሳዝናል:: (ኤፌ. 4:30) እራሱን ከእግዚአብሔር ይለያል? «. . . ጽድቅ ከአመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለው? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው? (2ቆሮ. 6:14) የሚለው በሙሉ ይመለከተዋል:: እግዚአብሔር ብርሃን ነው ኃጢአት ደግሞ ጨለማ ነው:: ኃጢአተኛ ስራዎቹ መጥፎ ናቸውና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የሚወድ ነው:: (ዮሐ. 3:19)



### ከእግዚአብሔር መለየት አያስፈራችሁምን? ከእርሱ ተለይቶ በጨለማ ውስጥ መኖርስ?

አባካኙ ልጅ ከአባቱ ተለይቶ ነበር:: «ወደ እሩቅ ሀገር ሄደ» (ሉቃስ 15:13) አባታችን አዳም ኃጢአትን በሰራ ጊዜ ከ እግዚአብሔር ተለይቶ ነበር:: በዛፎችም መካከል ተደበቀ:: (ዘፍ. 3:8) ኃጢአት በእውነት በእግዚአብሔር መካከል ገደብን ይሰራል:: አንድ ሰው እግዚአብሔርን ወይም ከእግዚአብሔር የሚለየውን ኃጢአት መምረጥ አለበት::

ኃጢአተኛ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዳለ ጠንቅቆ ያውቃል ነገር ግን ንስሐ ሲገባ ወደ እግዚአብሔር እየቀረበ እንደሆነ እና ከእርሱ ጋር እየተገናኘ እንደሆነ ያስባል:: ነገር ግን የቅድስና ኑሮን እየመራ ከሆነና እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እርሱ ደግሞ በእግዚአብሔር ውስጥ እየኖረ ከሆነ ጌታችን «እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል::» (ዮሐ. 15:5) ይላል:: በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፉ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል . . .» (ዮሐ. 15:6) ይሄ አስፈሪ አይደለም?

ይሄም ኃጢያተኛውን ያስፈራ ይሆን? ኃጢያተኛውን የሚያስፈራው ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር የማይስማማ መሆኑ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ» (2ቆሮ. 5:10) እያለ ለሁሉም ሰው ጥሪ ያቀርባል::

ቀላል ግጭት ሳይሆን በጣም ትኩረት የሚሰጠው ነገር ነው:: «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንደሆነ አታው

www.ethiopianorthodox.org

ቁምን? (ያዕ. 4:4) ይላል ቅዱስ ያዕቆብ:: ይህንን ቅዱስ ዮሐን ስም «. . . ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለምም:» (1ዮሐ. 2:15) በማለት ይደግፈዋል:: ስለዚህ ኃጢአት ኃጢአተኛው ለእግዚአብሔር ያለው አመለካከት ነው:: ለእግ ዚአብሔር ምንም ፍቅር አክብሮት . . . የለውም:: በእርግጥ ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ነው:: አንድን ሰው ከእግዚአ ብሔር መገኘት ውስጥ እንዲወጣ ማድረግ ነው::

«ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ. . .» (ማቴዎስ 7:23) በማለት ጌታችን የተናገራቸው ሰዎችን ምን ያህል ያስፈራቸው ይሆን? «ከእኔ ራቁ» የሚለውን ሰምቶ የሚቋቋምና የማይፈራ ማን ይሆን? ጌታችን በሩን ከዘጋባቸው ሞኝ ደናግል ጋር ይህ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው:: «እውነት እላች ኋለሁ አላውቃችሁም» (ማቴ. 25:12) ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት:: እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ. . .» (ዘፍ. 4:13-14) በማለት ቃየን እያለቀሰ ከተነገረው ጋርም ተመሳሳይ ነው::

እግዚአብሔር «እናንተ ክፉ አድራጊዎች ከዚህ ሂዱ እኔ አላወቃችሁም» ይላቸዋል:: ለምን? ምክንያቱም ሰውየው ከእግ ዚአብሔር ይልቅ ዓለምን ወዶአል:: እስጢፋኖስ ለአይሁድ እንደ ተናገረው የእግዚአብሔርን መንፈስ አሳዝኖታል ብሎ በመወቀሱ ተቃውመውታል:: (ሐዋ. ሥራ 7:51) ከላይ እንደተመለከትነው ቃየል ከእግዚአብሔር በመለየት የእግዚአብሔር ተቋዋሚና ጠላት ሆኗል::

የዚህ ሰው ህሊና ሲነቃ እግዚአብሔርን በመፍራት «አንተን እቋቋምህና ጠላትህ እሆን ዘንድ እኔ ማነኝ? የእግዚአ



ብሔርን መንፈስ አሳዝንና ትዕዛዙን እጥስ ዘንድ እኔ አቧራውና አመዱ ማን ነኝ? እርሱን ዕቃወምና ስልጣኑንና መንግስቱን እፈታተን ዘንድ እኔ ማን ነኝ?» ይላል:: በዚህ ጠላትነትና በእምቢተኝነት መቀጠል ስለማይችል ይፈራል:: ለእግዚአብሔር ቁጣ ከተጋለጠ ደግሞ ይጠፋል::

የኃጢአትንም መዘዝ ይፈራል:: ኃጢአት ውስጣዊ ሰላ ምን ሊያሳጣው የሚችል ጭንቀቴ ደክሜያለሁ «ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ በእንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ::» (መዝ. 6:6) ይላል:: «አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ» (መዝ. 6:2):: ዳዊት እንዳለቀሰው ጴጥሮስም አልቅሷል:: «ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ለቅሶ አለቀሰ::» (ማቴ. 26:75) ተብሎ ተፅፏል::

ቅዱሳን ከኃጢአት የተነሳ እንደተሰቃዩ ሁሉ ክፉዎችም ይሰቃዩ ነበር:: ለዚህ ምሳሌያችን ከሀዲው የአስቀሮቱ ይሁዳ ነው:: በመንፈሱ ተጨንቆ ነበርና ሳንቲሙን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወርውሮ በመሄድ እራሱን ሰቀለ:: (ማቴ. 27:5) ስለዚህ በኃጢአቱ ምክንያት ሞተ:: ጲላጦስ ወደቤቱ በተመለሰ ጊዜ «... እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንፁህ ነኝ . . » (ማቴ 27:24) እያለ እጁን ታጠበ::

የአንዳንድ ሰዎች ስቃይ ሌሎች ሰዎችን ኃጢአታቸውን ያስታውሳቸዋል:: ይህ በተራው እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይመራቸዋል:: ለምሳሌ አንድ ሰው በሙያው ውድቀት ሲገጥ መው «ይህ ከኃጢአቴ የተነሳ ነው» ሊል ይችላል:: ከዚህ በኋላ እርሱ ወይም ወዳጁ ቢታመም ኃጢአቱን በማስታወስ «ምክንያቱ ኃጢአቴ ነው» ይላል:: እንደገና ተደጋጋሚ ችግር ሲገጥመው ይችላል ስለዚህ ለራሱ «ይህ ከበዛው ኃጢአቴ

www.ethiopianorthodox.org

የተነሳ ነው» ብሎ ይነግረዋል:: እነዚህ በሙሉ ከሰማያዊው ዘላለማዊ ቅጣት ባሻገር ያሉ ምድራዊ ቅጣቶች ናቸው:: እነዚህ በሙሉ በዘዳግም መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱት መርገምቶች ያስታውሱና::

ህጉን ለሚጥስ ሰው በሙሉ «እግዚአብሔር ከጠላቶችህ ፊት የመታህ ያደርግሃል:: በአንድ መንገድ ትወጣባቸዋለህ በሰባት መንገድ ከእነርሱ ትሸሻለህ ለምድርም መንግስታት ሁሉ ድንጋጤ ትሆናለህ:: ራስህ ለሰማይ ወፎች ሁሉ ለምድር አራዊት መብል ይሆናል የሚያስፈራቸው የለም:: እግዚአብሔር ፈውስ በሌለው በግብፅ ቁስል በእባጭም በቋቁቻ በችፌም ይመታል:: እግዚአብሔር በእብደት በዕውርነት በድንጋጤም ይመታሀል:: በቀትር ጊዜ ዕውር በጨለማ እንደሚርመሰመስ ትርመሰመሳለህ መንገድህም የቀና አይሆንም በዘመንህም ሁሉ የተጨነቅህ የተዘረፍህም ትሆናለህ የሚያድንህም የለም::» (ዘዳ. 28:25-29) በማለት ይናገራል:: «. . .ሁልጊዜ የተጨነቅህ የተገፋህም ትሆናለህ::» (ዘዳ. 28-33) በማለት ይህንን እርግማን ይደግመዋል::

ከእነዚህ ቅጣቶች የሚጠቀምና እግዚአብሔር መፍራትን የሚያገኝ ሰው የተባረከ ነው:: እነዚህ ቅጣቶች ወደ ንስሀ ስለሚመሩት እግዚአብሔር በመፍራት ይኖራል:: የማይጨነቅ ግድ የለሽ ሰው ግን ልቡ ይደነድንና ይጠፋል:: ሰውን በምድር ላይ የሚገጥሙት ችግሮችና ቅጣቶች «ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» (ሚል. 3:7) የሚለውን ድምፅ ያስተጋባል:: «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት በማስመረር እንደሆነ ልባችን እልከኛ አታድርጉ::» (ዕብ. 3:15) ብሏል:: ሐዋርያው



ጳውሎስ:: እንደገና «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ:: እግዚአብሔር እንደተፈጠሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራምና» (ሮሜ. 20-22) ይላል::

ስለዚህ ለምን እራሳችሁን ከእግዚአብሔር ወደ መለየትና ወደ መገለል ቅጣት ትመራላችሁ? ኃጢአትን ሳይሰሩና እግዚአብሔርን እየፈሩ መኖር አይሻልምን? በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መኖር አለብኝ ካላችሁ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ፍርድ አስቡ:: ቅዱስ እንደሆነና ቅድስናው ገደብ የለሽ እንደሆነም አስታውሱ:: ለቅድስናቸው ገደብ ያላቸው ሰዎች በኃጢአት ከተናደዱ ለቅድስናው ገደብ የሌለው እግዚአብሔርስ? ዮሴፍ በኃጢአት ጊዜ «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ. 39-9) በማለት አምልጧል:: እንደቀላል ነገር ሳይሆን እንደ ትልቅ ኃጢአት ነበር የቆጠረው::

በሰዎች ፊት ኃጢአትን መሥራት ትፈራለህ በመላእክት ፊት ደግሞ ከዚህም በላይ ትፈራለህ በእግዚአብሔር ፊትስ? ችግሩ እግዚአብሔርን ከፊታቸው እንዳላስቀደሙ ሰዎች ኃጢአትን ስፈጽም የእግዚአብሔርን መገኘት አለማወቅ ነው:: መዝሙረኛው ዳዊት «እግዚአብሔር በፊታቸው አላደረጉትም» (መዝ. 54:3) በማለት ይናገራል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን አንፈራና ኃጢአትን ትፈፅማለህ:: ምክንያቱም እንደማናይህ በማሰብ እግዚአብሔር በአይምሮህ ውስጥ የለም::

ሰውን እንደምትፈሩ እግዚአብሔርን ፍሩ:: በሰው ፊት እንደምታፍሩ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊትም እፈሩ:: ሰዎች ለእናንተ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው ስለምትፈልጉ በድብቅ የሚፈጽም ኃጢአት በግልፅ መፈፀም አትችሉም:: በድ

www.ethiopianorthodox.org

ብቅ የምንፈፅመውን በሙሉ የሚያየው እግዚአብሔርን ግን ትኩረት አንስጠውም ደግሞም አምላካችንን አንፈረራም:: ለምን ድነው በእግዚአብሔር ፊት ለምታሳዩት ባህሪ በሰው ፊት እንደምታሳዩት ባህሪ የማትጠነቀቁት? ይህ እግዚአብሔርን ስለ ማትፈሩ ነገር ግን ሰውን ስለምትፈሩ ነው:: ወደ ግብዝነትና ሰዎችን ወደማታለል የሚወስደውን በሰዎች ፊት ቅዱስ መስሎ መታየትን ትወዳላችሁ:: በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን መሥራት በማትፈሩበት ሰአት አንድ ትንሽ ህፃን እንዳያያችሁ ግን ትፈራላችሁ:: ሠራተኛችሁ ወይም እናንተ የቀጠራችሁ ሰው እንኳን እንዳያያችሁ ትሰጋላችሁ::

የምትሰሩት ነገር ወይም የምትናገሩት ነገር በሰዎች ዘንድ የሚያካስሳችሁ ከሆነ እንዳትቀረፁ ወይም እንዳትቀዱ የምትፈሩበት አጋጣሚ አለ:: ስለዚህ በሰዎች ፊት በጣም ጠንቃቃ ሰው በሌለበት ደግሞ ግድ የለሽ ትሆናላችሁ:: ሰው በማያይበት ወቅት የእግዚአብሔር አይኖች ያያሉና ይህ እግዚአብሔር እንደማትፈሩ ማስረጃ ነው::

እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ለመድረስ በሰዎች ፊት ማድረግ የምንፈራውን ነገር በድብቅ አለማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው:: በሰዎች ፊት ልትገልፁት የማትችሉት ምንም አይነት አስተሳሰብ አይኑራችሁ:: «ሀሳቦቼን የሚፈትነውንና የሚያውን የልቤንም መሻት የሚፈትነውን እግዚአብሔርን ማፈር አለብኝ:: ከውጭ በኩል በጣም ነጭ እንደሆነ ከውስጥ ግን በአጥንትና ንፁህ ባልሆነ ነገር እንደተሞላ መቃብር መሆን የለብኝም» በማለት ለራሳችሁ ንገሩት:: ጌታችን ጻፎችንና ፈሪሳውያንን በእነዚህ ቃላት ነቅፏቸዋል:: (ማቴ 23:27)



ከዚህ በኋላ በሌሎች ፊት ቅዱስ የሆናችሁትን ያህል በራሳችሁ ፊት ቅዱስ ለመሆን ሞክሩ:: በሌሎች ቢገለጥ ሲያሳፍራችሁ የሚችል ሥራችሁንና ፍላጎታችሁን አስወግዱ:: በሌሎች ፊት ስለ ሥርዓት ትኩረት በሚሰጡ ቅዱሳን ፊት ማለቴ ነው:: ስለዚህ ከእነርሱ እግዚአብሔርን ስለመፍራት ትማሩ ዘንድ ቅዱሳንን ጓደኞቻችሁ አድርጉዋቸው:: በእነርሱ ፊት ልታደርጉ የማትፈልጉት ነገር እነርሱ ሳይኖሩም ሲቀር አለማድረግ ባሕሪያችን ይሆናል::

ሳታውቁት ልክ እንደነርሱ ልትሆኑ ስለምትችሉ እግዚአብሔርን የማይፈሩና ግድ የለሽ የሆኑ ሰዎችን ጓደኛ አታድርጉዋቸው:: ጥንቃቄን ለሁሉ ነገር ትኩረት የምትሰጡ መሆናችሁን በመመልከት ሊሳለቁባችሁ ይችላሉ:: ከዚህ በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ በጣም እየራራ እንደሆናችሁ ሊሰማችሁና የኃጢአትን ፀያፍነት ልትረሱ ትችላላችሁ:: በመቀጠልም ግድ የለሽን እግዚአብሔርን የማትፈሩ ትሆናላችሁ::

እግዚአብሔርን ወደመፍራት ለመድረስ ቅጣቱንና አስፈሪውን ፍርድ በአይምሮአችን ውስጥ ማስቀመጥ አለብን:: ቅጣትን መፍራት የሰው ተፈጥሮ ነው:: ያለዚህ ፍርሃት ኃጢአት በሁሉም ቦታ ሊስፋፋ ይችላል:: ክፋውን ስራ እንደመገድቢያ ነው:: ቅጣትን መፍራት በአባታችን አዳም የተጀመረ ነው:: ኃጢአት በሠራ ጊዜ ፈራና በዛፎች መካከል ተደበቀ:: ፍርሃት በቅዱሳንና በነቢያት ዘንድ ሳይቀር በእርሱ ትውልድ ዘንድ ቀጥሏል:: እግዚአብሔርን እርሱን ወደመፍራትና ወደንስሐ ይመለሱ ዘንድ ሕዝቡን መቅጣት ቀጠለ::

www.ethiopianorthodox.org

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ቅጣቶች ተጽፈዋል:: በብሉይ ኪዳን ላይ የተጠቀሱትን ቅጣቶች ወይንም በዚያ ላይ የተዘረዘሩትን እርግማኖች ብቻ ማለቴ አይደለም:: (ዘዳ. 27:13) በ(ራዕይ ም. 8) ላይ የተጠቀሱትን ቅጣቶች ወይንም ጭንቀቶች ማለቴም አይደለም:: ደግሞም የፀጋና የዕውነት ኪዳን በሆነው በአዲስ ኪዳን ላይ በጌታችንና በደቀመዛሙርቱ የተጠቀሱትን ቅጣቶችም ብቻ ማለቴም አይደለም::

ነገር ግን የመጀመሪያው መለኮታዊ ትዕዛዝም በቅጣት የታጀበ ነበር:: ይህ ማለት ለአዳምና ለሔዋን የተሰጠው የመጀመሪያ መለኮታዊ ትዕዛዝ ትዕዛዜን ስላልጠበቅህ «ሞትን ትሞታለህና::» (ዘፍ. 2:17) በሚል ቅጣት የታጀበ ነበር:: ይህ ትዕዛዝ ዝነኛ ለሆኑ አዳምን ሄዋን ለተባሉ ሰዎች የተሰጠ ነበር:: እነዚህ ሰዎች ከአሁን ሰው ይልቅ የበላይ የነበሩ በጣም ንፁህ የነበሩና የኃጢአት እውቀት የሌላቸው ነበሩ:: እራቁታቸውን ሳሉም የማይተፋፈሩ ነበሩ::

እግዚአብሔርን ይህንን ቅጣት በአምሳሉ በፈጠረው ሰው ላይ ፈፅሟል:: ከንፁህ አዳም ጋር በፍቅር ሲያወራ የነበረው እግዚአብሔር አዳም ኃጢአት ከሠራ ከፈራው ጋር አንድ አይነት ነው:: እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በቀጣይ ከገነት አስወጣቸው:: የህመምንና የድካምን ቅጣት ጣለባቸው እርሷም ሰውን ያሳሳተውን እባብ ሸኮና እንድትቀጠቅጥ ተደረገች:: (ዘፍ. 3:15-19)

እግዚአብሔር አዳምን ሲቀጣው «. . . አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና::» (ዘፍ. 3:19) ብሎ አለው:: ምናልባት በአዳም አዕምሮ ውስጥ ጥያቄ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል::



«እግዚአብሔር ሆይ እኔ አፈር ነኝ? በአምሳልህ የተፈጠርኩ አይደለሁምን?» ሊል ይችላል:: «ከዚህ በኋላ የእኔ አምሳል አይደለህም:: ንፁህ በነበርህ ጊዜ የእኔ አምሳል ነበርህ:: ኃጢአትን ካሰብህ በኋላ ግን ይህንን አምሳልነት አጥተሀል:: አፈር እንደነበርህ ወደ አፈር ትመለሳለህ::» ብሎ እግዚአብሔር መልሶለት ይሆናል::

② **ቅጣት ለሰው ልጅ ጠቃሚ ነው:: እግዚአብሔር እኛን ለማንቃት ነው ያመጣው::**

እግዚአብሔር ቀላል ለሚመስሉ ኃጢአቶች ሳይቀር ቅጣት አዘጋጅቷል:: «እኔ እላችኋለሁ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል:: (ማቴ. 12:36)

ከማንም አፍ ዘንድ የሚወጣ አንድ ፀያፍ ቃል በሰውየው ላይ ትልቅ ፍርድ ያስከትላል:: «. . . ከቃልህም የተነሳ ትኮነናለህ::» (ማቴ. 12:37) ይላል መጽሐፍ ቅዱስ:: «. . . ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም::» (1ኛቆሮ. 6:10) ስለሚል አንድ ሰው ከስድብ የተነሳ መንግስተ ሰማይን ሊያጣ ይችላል:: እነዚህ ተሳዳቢዎች ከአመንዝራዎች ከሴሰኞች ከጣኦት አምላኪዎች ጋር በአንድ ምድብ ውስጥ ነው የተቀመጡት:: (ያዕ. 5:12)::

ስለዚህ አንድም ኃጢአት የሰውን መጥፋት ሊያስከትል ይችላልና እግዚአብሔርን መፍራት በልባችን ውስጥ ይኑር:: «ህግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም

www.ethiopianorthodox.org

ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል. . .» (ያዕ. 2:10) ይላል መጽሐፍ ቅዱስ::

ስለዚህ ሐዋርያት «የቁጣ ቀን» የሚሉትን አስፈሪውን የፍርድ ቀንና የእግዚአብሔር ፍርድ እንፍራ:: «ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቀን ፍርድ በሚገለጥበት የቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ:: እርሱ ለእያንዳንዱ እንደስራው ያስረክበዋል. . .»(ሮሜ.2.5-6) «ለአመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአመጸ ኞች ላይ ግን ቁጣን መቅሰፍት ይሆንባቸዋል::» (ሮሜ 2:8-9) ይላል::

ስለዚህ ጌታችን እግዚአብሔር ስለመፍራት በአንድ አረ ፍተ ነገር ውስጥ 3 ጊዜ ተናግሯል:: ይህንን ቅጣት ለመቀልበስ ስልጣን ያለውን እግዚአብሔርን እና ገሀነምንና ፍርድን እድንፈራ አስተምሮናል:: «እንግዲህ ወደ እረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቷልን ከሆነ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ::» (ዕብ. 4:1) በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ፍርድን ስለመፍራና መዳን ስለማጣት ያወራል::

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ቃል በገባልንም ወደ ዘላ ለማዊው እረፍት መግባትን እንዳናጣ ግን ይፈራል:: «ከሰማያ ዊው ጥሪ ተካፋይ የሆናችሁ ቅዱሳን. . .» (ዕብ. 3:1) ብሏልና እያወራ ያለው ቃል ከተገባላቸው አማኞች ጋር ነው:: በእርግጥም ቅዱሳን ናቸው:: ነገር ግን ኃጢአት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ ስለዚህ አሁንም መፍራት አለባቸው::

«የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መስዋዕት አይቀርል ንምና የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቋማዊዎችንም ሊበላ



ያለው የእሳት ብርታት አለ::» (ዕብ 10:26-27) ይላል ቅዱስ ጳውሎስ::

ቅዱስ ጳውሎስ ፍርድን ስለመፍራት እየገለፀ የኃጢአት አሳሳቢነት ይገልፃል:: «የሙሴን ህግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ቢመሰክሩበት ያለርህራሄ ይሞታል የእግዚአብሔር ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ እርኩስ ነገር የተቆጠረ የፀጋውንም መንፈስ ያክፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» (ዕብ. 10:28-29) ይላል ቅዱስ ጳውሎስ::

ይሔ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ከእንቅልፋቸው እንዲነቁ የሚያደርግ ከባድ ቃል ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው::» (ዕብ. 10:31) እያለ ይቀጥላል::

አስፈሪው ሁኔታ በእግዚአብሔር እጅ ላይ መውደቅ ያለው በፍርድ ቀን መሆኑ ነው:: በዮሐንስ ራእይ ላይ «. . . ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መል እክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ በታላቅ ድምፅም የፍርዱ ሰአት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት ሰማይ ንና ምድርንም በሀርንም የውሀንም ምንጮች ለሰራው ስገዱለት አለ::» (ራዕይ 14:7) ይላል ቅዱስ ዮሐንስ:: ለምንድን ነው ይህ ፍርሃት? ምክንያቱ ምንድን ነው? መልአኩ «. . .የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና. . .» (ራዕይ 14:7) በማለት ይመልሳል::

የሚያስፈራው የፍርድ ሰአት ነው. . . ሕይወታችንን የምናዘጋጀው ለዚያ ቀንና ሰዓት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ቀን የሚለውን ስሙ የሚልክያስ መጽሐፍ ይለዋል «. . .

www.ethiopianorthodox.org

ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን . . .» (ሚል. 4:5) በመለኮታዊው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወቅት እንዲህ እንላለን «ደግሞ ምፅአቱ አስፈሪና በክብር የተሞላ ነው»

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ደግሞ ምፅአት እንዲህ ይላል «የሰው ልጅ መላእክትን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል በዚህ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፡፡» (ማቴ. 13:41-42)፡፡

በኢዩኤል መጽሐፍ ላይ እንዲህ ተብሎ ተፅፏል «. . . የእግዚአብሔርም ቀን ታላቅና እጅግ የሚያስፈራ ነውና ማንስ ይችለዋል?» (ኢዩ. 2:11) እንደገና «. . .ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል፡፡» (ኢዩ. 2:31) እያለ ኢዩኤል ይናገራል፡፡

«የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ የሰማይ ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል ምድርም በእርሱዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርን በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል?» (2ጴጥ. 3:10-11) ይላል ቅዱስ ጴጥሮስ፡፡

የኢሳይያስ መጽሐፍም ስለአስፈሪው ቀን እንዲህ ይላል፡- «እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ ኃጢአተኞችዋንም ከእርሷ ዘንድ ሲያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በፅኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል፡፡» (ኢሳ. 13:9) ይሄ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነቢዩ ሆሴዕ በዚያን ሰዓት



ስለሚኖረው የህዝቡ ፍርሃት «. . .ተራሮችንም ክደኑን ኮረብቶችንም ውደቁብን ይሉአቸዋል፡፡» (ሆሴዕ 10:8) በማለት ይናገራል፡፡

እነዚህ ቃላት በዮሐንስ ራዕይ ላይ ስድስተኛው ማህተም በተፈታበት ሰዓት ተደግመዋል፡፡ «ስድስተኛውንም ማህተም በፈታ ጊዜ አየሁ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ ፀሐይም እንደ ማቅ ፀጉር ጥቁር ሆነ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ በለስም በብረቱ ነፍስ ተናውጣ ቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ ሰማይም እንደመጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፡፡ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ፡፡ የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለጠጋዎችም ኃይለኞችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች አለቶች ተሰወሩ ተራራዎችና አለቶችም በላያችን ወደቁ በዙፋ ንም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው» (ራዕይ 6:12-17)፡፡

ስለዚህ «ጌታችሁ በምን ሰአት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡» (ማቴ. 24:42) እያለ ጌታችን ይመክረናል፡፡ «ከሁለትም ይሰነጥቀዋል እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፡፡» (ማቴ. 24:51) እያለ ስለ ክፉው ባሪያ ይናገራል፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላል «እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰአት ይመጣልና» (ሉቃስ 12:40)

«ለነፍሳችሁ መዳን ንቁ፡፡ . . . በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ» (1ኛጴጥ. 1:17)፡፡ «ወገባችሁ የታጠቀ

www.ethiopianorthodox.org

መብራታችሁም የበራ ይሁን . . .» (ሉቃስ 12:35) የሚለውን ማስጠንቀቂያ በማስቀደም «. . . መቼ እንዲመጣ አታውቁ ምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ::» (ማርቆስ 13 :36) የሚለውን ምክር ያስከትላል ::

ንስሐ በመግባት እራሳችሁን ለአስፈሪው ቀን አዘጋጁ:: «. . . በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍፁምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ::» (ሮሜ 12:2) አልዓዛር እጆቹን ውሃ ውስጥ ነክሮ ምላሱን እንዲያቀዘቅዝለት የተመኘውን ሀብታሙን ሰው አስታውሱ :: (ሉቃስ 16 :24)::

አንዳንድ ሰዎች «ቀኑ ገና እሩቅ ነው ለምን እራሳችንን እናስጨንቃለን?» ይላሉ:: አንድ ነገር ልንግራችሁ እችላለሁ ምንም እንኳን የፍርድ ቀን እሩቅ ቢሆንም የመጨረሻው ቀናችሁ ግን መቼ እንደሆነ አታውቁም:: ስለዚህ መዳናችሁን በመፍራ ትና በመንቀጥቀጥ መፈፀም አለባችሁ:: (ኤፌ. 2:12) ያንን ቀን ያለምንም ተስፋ ከፍርሀት ወደ ንስሐ የሚመራን ተስፋ ይዞ መፍራት ይሻላል:: ይህንን ነው ቤተ ክርስቲያን በቀን በቀን የምታስተምረን::

## (3) ፍርድን መፍራት እና የሰውን ማንነት በሰው ሁሉ ፊት መግለጥ

እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን ሰውና መላእክትን በሙሉ ሰብስቦ ልክ የሰውን አስተሳሰብ ስሜት ዝንባሌ እና ግብዝነት በሙሉ እንደሚገልጥ ካሜራ ማንነታችንን በሰው ፊት ሁሉ ሲገልጥ ምን አይነት እፍረትና ፍርሃት ሊሰማን



እደሚችል አስቡት «እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገ የለም::» (ማር. 4:22 እና ሊቃስ 8:17) ብሏል ጌታ ኢየሱስ::

ስለዚህ በዛን ቀን እንዳትጋለጡ ከፈለጋችሁ ኃጢአታች ሁን ንስሐ ሊያጠፋው ይችላልና ንስሐ ግቡ (ሐዋ. ሥራ 3:19) ቤተ ክርስቲያን በጸሎታችን ጊዜ «በጻድቁ ዳኛ ፊት ቆሜያለሁና ከኃጢአቴ የተነሳ እፈራለሁ:: ነፍሴ ሆይ በመፈንጠዝ የታለፈ እድሜ ፍርድ ይገባዋልና በምድር ላይ እስካለሽ ድረስ ንስሀ ግቢ::» እንድንል ታስተምረናለች::

እንዲህ ብለንም እንፀልያለን:: «ነፍሴ ሆይ ይህ ሕይወት የሚያልቅ ይህ ምድር ደግሞ ዘላለማዊ ቢሆን ኖሮ ይቅርታን ታገኚ ነበር:: ነገር ግን በጻድቁ ዳኛ ፊት ክፋው ስራሽና ድርጊትሽ ጌታችን ሆይ ከአስፈሪው የፍርድ ቀን በፊት አሁን እፈራለሁ::» ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ንስሐና የእግዚአብሔርን ምህረት ወደመለመን ይመራናል:: በፍርድ ቀን ስንፈራና ስንንቀጠቀጥ እንዳንገኝ ግድ የለሽና ደካማ እንዳንሆንም የደርገናል::

ቤተ ክርስቲያን በእኩለ ሌሊት ጸሎት ላይ ጌታቸውን እየጠበቁ ስለነበሩት ብልጥና ሞኝ ደናግል ታስቀምጣለች:: ብልጦች ደናግሎች ለመግባት ችለው ነበር ሞኞች ግን ውጪ ቆዩ:: ጌታችን «. . .አላውቃችሁም. . .» (ማቴ. 25:12) አላ ቸው:: ምን አይነት አስፈሪ ቃል ነው:: ቤተ ክርስቲያን አስፈ ሪውን ደግሞ ምፅአቱን እያስታወሰችን ትጸልያለች:: በወንጌል ላይ እንዲህ የሚል ሌላ ክፍል አለ «ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምን እንግዲህ ንቁ::» (ማቴ. 25:13 እና ሉቃስ 12:40)

www.ethiopianorthodox.org

የብልጦቹንና የሞኞቹን ደናግል ታሪክ ባስታወስን ጊዜ «ነፍሴ ሆይ ያንን አስፈሪ ቀን አስቢ።» ሙሽራው ሆይ ጠብቀኝ» ብለሽ የምታላቅሽበትን ጊዜ አታውቂምና ፍሪ መፍራቱንም ሁልጊዜ አብሪ። ነፍሴ ሆይ እንደአምስት ሞኝ ደናግል ተዘግቶብሽ እንዳትገኚ አለመተኛትችን ተመልከቺ። ነገር ግን ጌታችን ከነዘይትሽ ትገናኚወ ዘንድ በጸሎት ትጊ።» ብለን እንጸልያለን።

ፍርድን በመፍራት ቤተ ክርስቲያን ንቁና ዝግጁ እንድን ሆን ትጣራለች። «ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው. . .» (ሉቃስ 12:35-37)

ቤተ ክርስቲያን ፍርድን በመፍራት ወደ ንስሐ ትጠራና ለች። ፍርሃትንና ንስሐን ብቻ ሳይሆን እያሰቡ መጸለይንም ታስተምረናለች። «እጅግ ብዙ የሆነውን ክፉውን ሥራዬን ሳስብ አስፈሪው የፍርድ ቀን ወደ ልቤ ይመጣል። በመንቀጥቀጥም እሞላለሁ። ሰውን የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ ከአንተ ዘንድ እጠለላለሁ። ኃጢአት የሌለበት ማን ነው? ፊትህን እንዳታዞር ብኝ እለምንሃለሁ። ለምስኪኗ ነፍሴ አንተን መፍራትን አስተ ምራት። ፍፃሜው ከመምጣቱ በፊትም አድነኝ።» ብለን እንጸልያለን።

እግዚአብሔርን ከመፍራት የተነሳ ቤተ ክርስቲያን ምህረ ትን እንድንለምን ታስተምረናለች። «ጌታ ሆይ ስቃዬን በርህራሄ ተመልከት። ሕይወቴ ወደ ፍፃሜ ቀርቧል። በስራዬም ውስጥ



ጽድቅ የለም። ስለዚህ በርህራሄ ትመለከተኝና ታድነኝ ዘንድ እለምንሃለሁ።» ብለን እንለምናለን።

«ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ እኔ ኃጢያተኛው ወዴት ልታይ?» ብለን እንድንጸልይ ቤተ ክርስቲያን ታስተምረናለች። ይህ ጸሎት በ1ኛ ጴጥሮስ ላይም ተጽፏል። «ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ አመፃኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?» (1ጴጥ. 4:18)።

ይህ ቃል ከጻድቃን ጋር እንድንቆጥር እንድንተጋና እንድ ንፈራ አያደርገንምን? ቤተ ክርስቲያን ከመፈራቷ የተነሣ ጌታ ማረን ብለን በእያንዳንዱ ጸሎት ወቅት 41 ጊዜ እንድንል ታስ ተምረናለች። የእግዚአብሔር ምሕረት መለመን እግዚአብሔርን መፍራታችን ማረጋገጫ ነው። የእግዚአብሔርን ምሕረት ያለ ፍርሃት እንጠይቃለን? በጭራሽ ። ስለዚህ «ሥጋዬ አንተን ከመፍራት የተነሳ ደነገጠ. . .» (መዝ. 119-120) ብለን እንጸልያለን።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ መንገድ እግዚአብሔርን መፍራትን አያስተማረችና በጸሎት እየተጋች እንድትኖር እንዲያውም የቀ ረውን ዘመናችንን ሁሉ በሰላም እና አንተን በመፍራት መኖርን ስጠኝ ብለን የምንጨርሰውን የቀንበቀን ጸሎትንና የቤተ ክር ስቲያንን ስርዓት ቅዳሴን በምስጋና ጸሎት እንድንጀምር ታደርገናለች።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በመቅደሱ ፊት ሰግደን እንዲህ እንላለን «እኔ ግን በምህረትህ ብዛት ወደ ቤት እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስና መቅደስ እሰግዳለሁ።» (መዝ. 5:7) ቄሱ ይህን ቃል መንበሩን ሲያጥኑ ይደጋግሙታል። ብዙ

www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን ጸሎቶችና ቅዳሴዎቹ እግዚአብሔርን መፍራት በውስጣቸው የያዙ ናቸው::

በምሽት ጸሎት ወቅት ቄሱ በማይሰማ ጸሎቱ ኦ ክርስ ቶስ ትልቅ አምላክ እና የምትፈራ እያለ ይጸልያል በፍታት ጊዜ «አንድ አድርገን አንተን በመፍራት አሳድገን ቅዱስ ወደ ሆነው ወደ አንተ ሀሳብ ምራን» ይላል::

ዲያቆኑ ወንጌሉ ከመነበቡ በፊት እግዚአብሔርን በመፍ ራት ቁሙ ይላል ምዕመናኑ በሙሉ ይነሳሉ:: ቄሱም አክሊላ ቸውንም ያወልቃሉ የእግዚአብሔር ቃል በፍርሃት ልንሰማ ይገባናል:: ለምን? ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃል እንዳላከ ብር በእርግጠኝነት እናውቃለን የእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይፈረድብናል አምላክ እንዲህ ይላል «የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው እኔ የተናገርኩት ቃል እርሱ በመጨረሻ ይፈረድበታል» (ዮሐ. 12:48):: መጽሐፍ ቅዱስ እየተነበበ መፍራት የሚለውን ቃል ስንሰማ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ሲኖር ዲያቆኑ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመፍራት እና በመንቀጥቀጥ ለእግዚአብሔር ሰገዱ ይላል::

ሙሴም አስርቱን ትዕዛዛት ሲቀበል እንዲህ ብሏል:: እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጣለሁ (ዕብ. 12:21) እንዲሁም አምላክ ለቅዱስ ዮሐንስ ሲገለጥለት እንዲህ አለ «ባየሁት ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ ቀኝ እጁንም ጫነብን አትፍራ ፊተኛው እና መጨረሻው ከዚያውም እኔ ነኝ» (ራእይ 1:17) እግዚአብሔርን መፍራት ቅዱስ ለሆነ መስዋዕት አጋዥ ይሆ ናል:: ስለዚህም ያለነቀፋ ልንሰጥ ወይም ልንቀበል እንችላለን::



በማስታረቅ ጸሎተ ወቅት ቄሱ «ነቀፋ ሳይ ሳንወይቅ ይህንን ሰማያዊ ስጦታ መቀበል እንድንችል እርስ በእርሳችን በተቀደሰ መሳሳም እንድንሳሳም እርዳን» ይላሉ:: ቄሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምፅአት ሲገልፅ «ዳግም ምፅአቱ በፍርሃትና በክብር የተሞላ ነው::» ይላል:: እግዚአብሔርን መፍራትን የምናገኘው ራሳችንን በመፈተሽና የእግዚአብሔርን ቃል በማስ ታወስ ነው «ስራህን አውቃለው. . .» (ራዕይ 2:3) እንዲሁም እግዚአብሔርን መፍራትን በመፀፀትና ራስን በማዋረድ እናገኛ ለን::

አንድ ሰው ኃጢአቱ ምን ያህል አፀያፊ እንደሆነ የማያ ውቅ ከሆነ እግዚአብሔርን መፍራት በልቡ ውስጥ አይኖርም ማለት ነው:: በሌላ በኩል አንድ ሰው ራሱን በመፈተሽ ጥንቃቄ ኃጢአቱ ምን ያህል ከባድና ብዙ እንደሆነ የሚሰማው ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔርን መፍራት በልቡ ውስጥ አለ ማለት ነው::

እግዚአብሔርን መፍራትን የምናገኘው ለእያንዳንዱ ለም ንሰራው ለምንናገረው ለምናስበው ለሚሰማን ስሜት እንደሚገ ባን ስንጠነቀቅና ለምንሰራው ስህተት ምክንያት መጸረር ስናቆም ነው:: ይህ ፍርሃት ጥንቃቄን ያመጣል ጥንቃቄ ደግሞ ፍርሃትን ያመጣል:: አንዱ ሌላውን ያጠናክራል:: ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለ ግንኙነት በጣም የሚያስገርመው በሚያደርጉት ጥፋት በጣም አድርገን እንወቅሳቸዋለን ነገር ግን ራሳችንን እነርሱን እንደምንወቅሰው ያህል አንወቅስም:: እዲያውም ራሳችንን ላን ወቅስ ሁሉ እንችላለን::

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው::» (ምሳሌ 9:10) ስለዚህ የመንፈሳዊው መንገድ ጅማሬ የሆነውን

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርን መፍራትን ማግኘት ከፈለግን በየቀኑ ምን እየ ሰራን እየተናገርን እና እያሰብን እንደሆነ ልናስተውል ይገባል:: ይህንን ነበር ቅዱሳን የሚያደርጉት:: ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ወደልብህ ከገባ ከዚህም በኋላ በሚዛን ብትመዘን ራስህን ከትናት የቀለለ ሆኖ ታገኘዋለህ::

መንፈሳዊ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሳያድግ ሲቀር ያስባል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በቅድስና ሕይወቱን መምራት እንዳለበትና እንደሚጠየቅ ያውቃል:: «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌ 20:26) ጌታችን ኢየሱስ በተራራው ስብከት ወቅት «እንዲሁ የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተም ፍፁማን ሁኑ::» (ማቴ. 5:48) ብሎ እንዳስተማረ እግዚአብሔር ፍፁም የሆነ ሕይወት እንዲኖረን ያዘናል::

ጀማሪ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጻድቅ ሰው ማሟላት ያለበት ነገር እንዳሟላ ስሚያውቅ ኃጢአት መሥራት ይፈራል:: በዚህ መንገድ ራሱን የሚገስፀው ስለ ሠራው ኃጢ አት ሳይሆን ነገር ግን ስላልፈፀመው ቅዱስ ስለሆነው ተግባር ነው:: ከዚህ በኋላ ከዚህ የበለጠ መስራት እንደሚችልና ብዙ ጥረት አድርጎ ብዙ ማግኘት እንደሚችል በተደጋጋሚ ራሱን ይጠይቃል ልክ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳደረገው (ፊሊ. 3:13)

እግዚአብሔርን መፍራት በውስጡ ያለው ሰው ኃጢያት መስራቱን ትዕዛዛቱን ስለመጠበቁ ወይም ስላለመጠበቁ ብቻ አይፈራም ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍቅር ያለምንም ገደብ ለማደግ ይታገላል:: ራሱን በመፈተሽ ጥንቁቅ አይሆንም ነገር ግን ንስሐ በመግባት ጭምር እንጂ::



ንስሐ መግባት እንዳለብን ካልገባንና የራሳችን ስህተት በሌሎች ላይ እያሳበብን ከሄድን እግዚአብሔርን መፍራት ማጣ ት በጣም ቀላል ነው:: እንዲሁም በንስሐ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ሳይሆን በቄሱ ፊት እንደቆምን የሚሰማን ከሆነ:: ለነገሩ ንስሐ በእግዚአብሔር ፊት ስንገባ ቄስ አብሮን ይሆናል እናም የእግዚአብሔር ይቅርታን በቄሱ አንደበት በኩል እንቀበላለን:: ይህንን ያልኩበት ምክንያት ብዙዎች በንስሐ አባታቸው ፊት ንስሐ ለመግባት ይፈራሉ:: ነገር ግን እግዚአብሔርን አይ ፈሩም::

ንስሐ በምንገባበት ወቅት ወይም በሌላ ጊዜ ኃጢአታ ችንን ለማስተባበል ስንሞክር እግዚአብሔርን መፍራታችን ከል ባችን መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ነው ኃጢአት የሆነውን ነገር ለማስተባበል ወይም የሰራነውን ኃጢአት በሌላ መንገድ በማየት አሳንሰን ማየት የለብንም ሁልጊዜ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ያለውን በማስታወስ «ራስን በነገር ሁሉ ከመውቀስ የተሻለ ነገር የለም» እናስተውል:: ይህ እግዚአብሔርን ወደመፍራት ይመራናል:: እግዚአብሔርን መፍራትን ለማግኘት ሁልጊዜ ጌታችንን በራእይ መጽሐፍ የተናገረውን «ሥራህን አውቃለሁ::» ያለውን አስታ ወስ:: ይህ ሐረግ ሰባት ጊዜ ተደግሟል:: እግዚአብሔር ለእያን ዳንዱ የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልአክ ይህንን ተናግሯ ዋል «ስራህን አውቃለሁ. . .» (ራዕ. 2:3) እያንዳንዱ ሰው ይህንን ቃል ሊያስተውለው ይገባል እንዲሁም በመጨረሻ የፍ ርድ ቀን ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ይህንን በሚለው በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆም ማወቅ አለበት::

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ መንገድ እግዚአብሔርን መፍራት ወደልባችን ውስጥ ይገባል ክብራችንን እንዳናበላሽ እያንዳንዱን ከሰው የደበቅናትን ኃጢአት እግዚአብሔር ያውቃል ለአንድ ኃጢአተኛ «ሌሎች አንተን ከመዳኘታቸው በፊት አንተ ራስህን ዳኝ» አሉት:: ሊታወቅ የማይቻል የተሸፈነ ነገር ስለማይኖር እራስህን ልታይና ልትፈትሽ ይገባል:: እግዚአብሔር «ስራህን አውቃለሁ» ካለ በሱ ፊት ንስሐ ልትገባና የመመለስ አቅም እንዲሰጥህ መጠየቅ አለብህ ማንም እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰይጣናዊ አሳብንም የሚፈራ የረከሰ ስሜትና ማንኛውም መጥፎ ሀሳብን ሰው የሚያስተውላቸውን እነኚህን ሁሉ እግዚአብሔር ያያቸዋል እንዲሁም ያውቃቸዋል::

እግዚአብሔርን የሚፈራ ማንኛውም ሰው ቅዱሳን መላእክት ቅዱሳንን ይፈራል እርሱም ጠባቂ መላእክትን ይፈራል በቤቱ የተሰቀሉትን የመላእክት ስዕል ሲመለከት ያፍራል ምክንያቱም የነሱ መንፈስ «ስራህን አውቃለሁ» የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ወደ እርሱ ያመጣልና::

ልክ እያንዳንዱን በኃጢአት የተሞላ ድርጊታችንን እና ምኞታችንን እንደሚቀረፅ መሳሪያ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን «የምትሰራውን በሙሉ አውቃለሁ» ይለናል:: ታዲያ ይህ እግዚአብሔርን ወደ መፍራት አይመራንም?

በልባችን ትህትና እግዚአብሔርን ወደመፍራት ልንደርስ እንችላለን:: ጻድቅ የሆነና ያለውን አቅም የሚያውቅ ሰው በኃጢአት ላይ እንደማይወድቅና ኃጢአት በእርሱ ቀሪ ስልጣን እንደሌለው ያስባል:: ጭምት የሆነ ሰው ሐዋርያው ጳውሎስ «ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ::»



(1ኛ ቆሮ 10:12) ብሎ የተናገረውን ያስታውሳል:: «ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ::» (ሮሜ. 11:20) ብሎ የተናገረውንም ያስታውሳል:: ስለዚህ ጥንቁቅ ሰው የሚያደናቅፍ ነገር ወዳለበት ስፍራም አይሄድም:: ኃጢአት ምን ያህል ሰዎችን እንደጣለችም ያስተውላል:: «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና እርስዋም ያጎደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው::» (ምሳሌ 7:26)

ስለዚህ እግዚአብሔርን በመፍራት ራሱን ይቆጣጠረዋል ጥንቁቅና የማይቀልድም ይሆናል:: ይህ ፍርሃት በራስ መተማመን እና የልብ ንፅህናን ያጎናፅፈዋል:: ማንኛውም ክፉ አስተሳሰብ ስር ሰዶ ችግር እንዳይፈጥርበት ገና ከመጀመሪያው ያስወግደዋል:: ቀበሮዎቹ የወይኑን ቦታ እንዳያበላሹት ይሰጋል (መኃ. 2:15)::

መሰናክሎችን በሙሉ ይፈራቸዋል ደግሞም ያስወግዳቸዋል:: ሁሉንም መሰናክል ማስወገድ የሚችል ኃይል እንዳለው አያስብም:: «ከዳዊት ወይም ኃጢአት ላይ ከወደቀው ጠቢቡ ሰሎሞን እና ከሌሎች ቅዱሳን በላይ አይደለሁም» ብሎ ይናገራል::

ጭምት የሆነ ሰው እድሜው እያረጀ ቢመጣ እንኳን እግዚአብሔርን መፍራትን ግን ከልቡ ውስጥ አያስወግድም:: በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ቢደርስ እንኳን እግዚአብሔርን መፍራትን ግን አይተውም:: መዝሙረኛው የጸሎት ሰው እና የተቀባ የነበረው የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት ምንም እንኳን የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ የነበረ ቢሆንም እርሱ ግን በኃጢአት ላይ ወደቀ:: (1ኛሳሙ. 16:13)፤ ስለዚህ

www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣን ጠንካራ የሆኑት ቅዱሳን ሳይቀር የሚያጠቃ ከሆነ እግዚአብሔር መፍራት በውስጣችን ሊኖር ይገባል::

ቅዱስ ጴጥሮስ በውስጡ እግዚአብሔርን መፍራት ስላልነበረ ለኢየሱስ «ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም . . . ከአንተ ጋር መሞት እንኳን የሚያስፈልገኝ ቢሆን ከቶ አልክድህም» (ማቴ. 26:33-35) አለው:: እንደገና «ጌታ ሆይ ወደ ወህኒም ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ» (ሉቃስ 22:33) አለው::

እግዚአብሔርን መፍራት በልቡ ውስጥ ያለው ሰው የእግዚአብሔርን እርዳታ እየለመነ ይፀልያል:: እራሱን በሚፈትሽበት ሰአት የኃጢአቱን ጥልቀት ይመለከታል ይቅርታንም እየለመነ ይጸልያል:: ድክመቱን ስለሚያስተውል እግዚአብሔርን መፍራት በልቡ ውስጥ አለ ስለዚህ ጠላት እንዳይገዛው እግዚአብሔር እንዲዋጋለት ይለምናል::

የንስሐ ሕይወት እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይመራሀል እግዚአብሔርን መፍራትም ወደ ንስሐ ይመራል ሁለቱም በአንድነት ይሰራሉ:: አንዱ ለሌላው መነሻና ውጤት ነው:: የንስሐ ሰው በፊት የነበረውን ድካሙን እና ለሰይጣን መገዛቱን በማሰብ ሁል ጊዜ ኃጢአቱ ከፊት ለፊቱ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርን በመፍራት ከኃጢአቱ የተነሳ ያለቅሳል:: ከመዝሙረኛው ዳዊት ጋር አብሮ «ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና . . .» (መዝ. 50:3) ይላል:: የንስሐ ሰው ልክ አልጋውን በእንባ እንዳረጠበው ዳዊት በጣም እያነባ ይጸልያል:: (መዝ. 6) ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖር ያስችለዋል::



## እግዚአብሔርን መፍራት ታላላቆቻችንን በማክበር እናገኘዋለን

አንድ ሰው ታላላቆቹን የሚፈራ ከሆነ ለምሳሌ ወላጆቹን አስተማሪውን ዘመዱን ቄሱን ወይም ደግሞ የሥራ አለቃውን ያለምንም ጥርጥር ከሁሉ በላይ የሆነውን እግዚአብሔርን መፍራትን ያገኛል:: አንድ ሰው የሚያየውን አባቱን ካልፈራ እንዴት የማይታየውን እግዚአብሔርን ሊፈራ ይችላል::

ያዕቆብ አባቱን መፍራትን አስታውስ /ዘፍ.31፣ ቁ.42/ አንድ ሰው አባቱን ካከበረና ለአባቱ ክብር ካለው በእርሱ ፊት ኃጢአትን አያደርግም እንዲሁም በብሉይ ኪዳን አንድ ትዕዛዝ አለ «ማናቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል አባቱን እና እናቱን ሰድቧልና ደሙ በራሱ ላይ ነው /ዘሌ ም.20 ቁ. 9/ እንዲሁም «በአባቷ የምታላግጥን የእናቷንም ትዕዛዝ የምትንቅን አይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጧታል አሞራዎችም ይበሏታል» /ምሳ. 30:12/ እግዚአብሔር ታላላቆችን እንድንታዘዝ ዝና ትዕዛዛቸውን እንድናከብር ያዘናል::

አንድ ሰው አድጎ እንኳን ማንኛውንም ነገር ከአባቱ ጋር ሲወያይ በታላቅ ክብር መሆን አለበት ከእርሱ ጋር እኩል እንዲሆን እያሰበ ማውራት የለበትም ነገር ግን ሁልጊዜ የአባትነቱን ክብር ሊያስተውል ይገባዋል::

በቀደም ጊዜ ከፍርሃታቸው የተነሳ ወጣቶች ታላላቆች ባሉበት ቦታ እንዲናገሩ አይፈቀዱላቸውም ነበር:: ይህንን አራት ጓደኞች ካሉት ነገር ግን አንዱ ዝም ሊል ለሶስቱ ብቻ ለብዙ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ካነጋገሩት ከቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ውስጥ እናገኛለን:: አራተኛው ጓደኛው የብዙዋዊ የባርክኤል ልጅ የሆነው ኤልሁ ነው በእርሱ ስህተት የተነሳ መናገር ግድ የሆነበት ኢልሁ እንዲህ አለ «እኔ በዕድሜዬ ታናሽ ነኝ እናንተ ግን ሽማግሌ ዎች ናችሁ ስለዚህ ሰጋሁ ዕውቀቴን እገልጽላችሁ ዘንድ ፈራሁ እንደዚህም አልሁ::» (ኢዮብ 32 ቁ. 6)::

በገዳም ሕይወት ብዙ ቅዱሳን ወጣቶች ታላላቆቻቸውን ለመመልከት አይኖቻቸውን አያነሱም ነበር አሁን አሁን በነጻነት እና በዲሞክራሲ ስም ለታላላቆች ያለው ክብር እየቀነሰ ነው:: ወጣቱ ትውልድ ህጉንና ትዕዛዙን እየተቀበለ አይደለም እግዚአ ብሔርን መፍራትንና ትዕዛዙን መቀበልን ስለጣሱት እንዲሁም ትዕዛዙን ከመጠበቅ ይልቅ ይከራከራሉ:: በሌላ በኩል ትዕዛዝንና ህጉን የሚቀበሉ ይህንን አያደርጉም::

በተመሳሳይ ሁኔታ አስተማሪውን የሚፈራ ተማሪ እንዲ ሁም አለቃውን የሚፈራ ወታደር ሁለቱም እግዚአብሔርን መፍራትን ይለምዳሉ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንደኛው ክፍለ ዘመን አስተማሪ በወንበር ላይ ይቀመጣል ተማሪዎች ደግሞ ከአስተማሪው እግር ስር ይቀመጣሉ ሐዋያው ቅዱስ ጳውሎስ በገማልያል እግር ስር እንደተማረ ይናገራል /የሐዋ.ሥራ 22:3/

ተማሪዎች አስተማሪያቸውን መፍራት ለምደዋል አሁን በትንሹ ተማሪው ለአስተማሪው ሲያወራ ለእሱ ያለው ክብር ለማሳየት በትንሹ መቆም አለበት አስተማሪው ቆሞ እርሱ መቀመጥ የለበትም በተመሳሳይ መንገድ የማርታ እህት ማር ያም ከክርስቶስ እግር ስር ተቀምጣ ቃሉን ትሰማ ነበር (ሉቃ.



10:39) የእግዚአብሔርን አገልጋይ የሚፈራ የዚያን አገልጋይ አምላክንም ይፈራል::

የእግዚአብሔርን መጋቢ የሚፈራ (ቲቶ. 1:7) እግዚአ ብሔርንም ሊፈራ ይገባዋል:: ምንም እንኳ ሳዖል ስህተት ቢሰ ራና ዳዊትን ሊቀድም ቢሞክርም እንዴት ዳዊት ሳዖልን ያከብ ረው እንደነበር እናያለን:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር የተቀባ ስለነበር ነው:: ስለዚህም ሳዖል በዳዊት እጅ በወደቀ ጊዜ ዳዊት ከመግደል ተቆጠበ እንዲህም አለ:: «እግዚአብሔር የቀባ ነውና እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት ዘንድ እግዚአብሔር ያርቀው (1ሳሙ.24:6):: እግዚብሔር ስለቀባው ሳዖልን በጣም አድርጎ አከበረው «ጌታዬ እያለ እየጠራው እግሩ ስር ይንበረከክ ነበር (1ሳሙ. 24:8)::

የንስሐ አባቱን የሚፈራ ሰው በእርግጠኝነት እግዚአ ብሔርን ይፈራል:: ነገር ግን ተጠንቅቆ አለበለዚያ ግን ንስሐ በአንተና በንስሐ አባትህ መካከል ብቻ እንጂ በአንተ እና በእግ ዚአብሔር መካከል እንደሆነ አታስብም በኃጢአትህ የምታፈረው በንስሐ አባትህ ፊት እንጂ በእግዚአብሔር ፊት አይደለም ይህ ንን ክብር መስጠት ያለብህ አባት ለሆኑ ቄስ ብቻ ሳይሆን ለቅዱሳንም ጭምር ነው::

የሐዋርያትን ስም ስንጠራ በአክብሮት መሆን አለበት ለምሳሌ ጴጥሮስ ጳውሎስ አንልም ነገር ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ቅዱስ ጳውሎስ እንጂ አንዳንድ ጊዜ ይህ የአትናቴዎስ ትምህርት ነው እንላለን ነገር ግን በአክብሮት ልንጠራ ይገባናል እንደ ትልቅ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አትናቴዎስ ለቅዱሳን አክብሮት ሲባል

www.ethiopianorthodox.org

በፋሲካ ሁለት ወራት ወቅት የቅዱሳንን ድርሳን ለመቀበልና እና ለመጨረስ ቤተ ክርስቲያን ዝማሬ ታቀርባለች በድርሳኑ መጨረሻ እንዲህ እንላለን፡ አምሮአችንና ልባችንን በጠቃሚ ትምህርት ያበሩትን የቅዱሳንን ድርሳን እናጠናቅ እንላለን። በእውነቱ ምን አይነት አክብሮት ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን የምትሰጠው የጻድቃን መቀባትና ለህዝቡ በረከት ሲሆኑ ስንመለከት ለጻድቃን ምስል ያለንን ክብር እንገልጻለን ከጻድቃን ምስል ፊት ስናበራ ጻድቃን ለዚህች ምድር ብርሃን እንደነበሩ እናሳያለን እንዲሁም በክብረ በዓል ወቅት ቄሶች ታቦት ተሸክመው ከጻድቃን ምስል ፊት ዕጣን እያጠኑ በታላቅ አክብሮት ክብረ በዓሉን ያከብራሉ።

የጻድቃንን ስዕላቸውን ክብረ በዓላቸውንና ስብከታቸውን እንዲህ ካከበርን የዓለምን ፈጣሪ እግዚአብሔርን እንዴት በይበልጥ ማክበር አለብን አንድ ሰው ጻድቃንን ካከበረ ጠባቂ መላዕክቶችንም ያከብራል ማለት ነው። ጠባቂ መላዕክትን ብታከብር በእርሱ ፊት ኃጢአትን ለመሥራት ወይም የማይሆን ቃልን በእርሱ ፊት ለመናገር ታፍራለህ ለራስህ እንዲህ ትላለህ እንዴት ኃጢአት እሰራለሁ ጠባቂ መልአክ ያየኛል ኃጢአት ከሰራሁ ጥሎኝ ይሄዳል (በመዝ. ም.1 ቁ.1) «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልሄደ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለራስህ ታስታውሳለህ መላእክት በተዋረደ ስፍራ የተቀመጠውን ኂጢአተኛ መጥተው ስለስራው ገልጸው ንስሐ እንዲገባ ሊያደርጉት ይችላሉ ነገር ግን ኃጢአተኛው ከዚያ ስፍራ ወይም ከስራው የማይወጣ ከሆነ እዚያው ጥሎት ይሄዳል



ምክንያቱም ጻድቅ ከአመጻ ጋር ብርሃን ከጨለማ ጋር ህብረት የለውምና (2ቆሮ. ም.6 ቁ.14)። ጠባቂ መልአክ ጥሎኝ ይሄዳል ወይም ይተወኛል ብለን የምንፈራው ፍርሃት እግዚአብሔርን የመፍራት አካል ነው።

ተጠንቀቅ ጠባቂ መልአክ ለኃጢአትህና ለመጥፎ አስተሳሰብህ ሲል እንዲተውህ አታድርግ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አስታውስ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል» (መዝ.34:7) የእግዚአብሔር መልአክ ኃጢአተኛን ኃጢአት ለማየት ከአንተ ጋር አይቆምም። መላእክቶች ሆኑ ጻድቃን ኃጢአት ስትሰራ ሲያዩህ የምታፍር ከሆነ ከኃጢአትና መጥፎ መንገድ ራቅ ይህ ስሜት እግዚአብሔርን ወደመፍራት ይመራሀል ፍርሃታችን ዋጋንና ባህልን ሊይዝ ይገባል።

አንድ ሰው ለባህልና ለመመሪያዎች የማይጠነቀቅ ከሆነ ለእግዚአብሔር ህግጋትም አይጠነቀቅም በአባቱ በአስተማሪው በቀጣሪው በአስተዳዳሪው ላይ የሚያምፅ ትውልድ በእግዚአብሔር ስልጣንም ላይ ያምጻል ታላቁን የማያከብር ሰው በእግዚአብሔር ላይ ይቆጣል እናም እግዚአብሔርን መፍራት ያጣል ታላላቆቻችን መፍራት እና ማክበር ራሳችንን እናስለምድ ይህም እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይመራናል።

ቅዱስ ቦታዎችን በማክበርና ለእነሱ በመገዛት እግዚአብሔርን መፍራትን ታገኛለህ ለመጸለይ ስትነሳ በማን ፊት እንደምትቆም ማሰብ አለብህ በነገሥታት ንጉሥ በጌቶችም ጌታ ፊት ነው የምትቆመው መላእክት ሱራፌል እና ኪሩቤል በሁለት ክንፋቸው አይናቸውን በሁለቱ ደግሞ እግራቸውን ሸፍነው

www.ethiopianorthodox.org

የሚያመልኩት እግዚአብሔር አስፈሪ አምላክ ነው:: ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ያመልኩታል «ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥር ሀልና ስለፈቃድህም ሁነዋልና ተፈጥረዋልምና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል» (ራዕይ. ከ10-11) እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ ስትጸልዩ በልባችሁ እግዚአብሔርን መፍራታችሁ ወዴት አለ? በአለቃ ፊት በአክብሮት እና በፍር ሃት እንደምትቆመው ትቆማለህ? ታላቁ መምህር ይስሀቅ በጸ ሎት ወቅት እግዚአብሔርን ስለመፍራት እንዲህ ብሏል «በእግ ዚአብሔር ፊት ለጸሎት ስትቆም ልክ የእሳት ፍም አጠገብ እንደቆምክ አስብ::»

አባታችን አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም እንዲህ ብሏል:: «እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ . . .» (ዘፍ 18:27) በጸሎት ወቅት ከአባትህ ጋር ታወራለህ? ልክ ነህ ነገር ግን እሱ እደማንኛውም አባት አይደለም ነገር ግን አምላክ እንዳስተማረ «በሰማይ የምትኖር አባታችን» እንላለን ስለዚህ አስታውሱ የእግዚአብሔር ዙፋን በሰማይ ነው (ማቴ. 5:34) ስለዚህ ስንጸልይ የእግዚአብሔር ዙፋር በሰማይ እንደሆነ እያስታወስን አይኖቻችን ወደ ላይ እናነሳለን::

ቅዱስ ማር ይስሀቅ በጸሎት ወቅት መኖር ስላለበት ስርዓትና አቋቋም እንዲህ ይላል:: «በጸሎት ወቅት በማን ፊት እንደምትቆም ገብቶህ በአክብሮት ቁም ቀጥ ብለህ ቁም እጅህንና አግርህን አታንቀሳቅስ እንዲሁም ሀሳብህ ወደሌላ ቦታ እንዳ ይሄድና በሌላ ነገር ትኩረትህ ተወስዶ ፀሎትህ እንዳይቋረጥ አድርግ:: አሁንም አሁንም ለእግዚአብሔር ያለህን ክብር ለመግ



ለጽ ለእግዚአብሔር ለምታወራው ነገር ትኩረት በመስጠት በመስገድ ወይም እጅ በመንሳት እግዚአብሔርን አምልክ::» ቅዱስ ማርይስሀቅ ዋናው አስፈላጊ ነገር ሀሳብንና ስሜትን በአንድ ላይ መያዝ እንደሆነ ይናገራል::

አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ጠየቀ ሀሳቤ ከእግዚአብሔር ውጪ እያሰበ ለምን እጸልያለሁ? እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት ምክንያቱም እግዚአብሔር መፍራት የሌለበት ጸሎት ነው:: እግዚአብሔርን መፍራት በልብህ ፅኑ ከሆነ በማስተዋልና ሀሳብህ ከእግዚአብሔር ውጪ ሳይሄድ ትፀልያለህ:: የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችሁ የእርሱን ክብር እንድትረሱ የሚያደርግ ነገር እንደሆነ አታስቡ «አዕምሮህ አርቆ ከተጓዘ ማተኰርን አለመደም ማለት ነውና ለአንድ ለተጨማሪ ጊዜ መልሰው::» በጌታ ላይ እንዲያተኩር አስተምረው::

እንዲሁም ማንም ያለእውቀት ባለማሰብ ወይም ምን እንዳለ ባለማስተዋል የሚጸልይ ይሆናል:: ነገር ግን እግዚአ ብሔርን መፍራት በልቡ ውስጥ የለም:: ያለትህትና ወይም ሀሳብህ ወደሌላ ነገር ሄዶ ወይም ቶሎ ለመጨረስ ብቻ ቶሉ ቶሎ በመጸለይ ልክ ከእግዚአብሔር ጋር ማውራት እንደሰለቸህ ሆነህ ወይም ሌላ አስፈላጊ ጉዳይ እንዳለህ ሆነህ ስትፀልይ በዚህ መንገድ እግዚአብሔርን ስታዋራ እግዚአብሔርን ያለመፍራትህን ያሳያል::

www.ethiopianorthodox.org

## እግዚአብሔርን መፍራት በጸሎት ወቅት ለእግዚአብሔር ክብር እንድትሰጥ ያደርጋል

እንዲሁም ትህትና በጸሎት ወቅት እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይመራናል:: ትህትና ለምሳሌ በጸሎት ወቅት የምንጠቀምባቸውን የትህትና መገለጫዎች ጸሎትን በምስጋናና በማድነቅ መጀመርን ያመጣል የእግዚአብሔርን ስም አክብሮት በተሞላ ፍርሃትና በክብር የሚጠራ ዝም ብሎ ኢየሱስ ኢየሱስ የሚል ሳይሆን ነገር ግን ልክ መልአክ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ በክብር ተሞልታለች» (ኢሳ. 6:3) ከጸሎት የተነሳ ምድር ትንቀጠቀጣለች::

እግዚአብሔርን መፍራት ልክ በጸሎት ጊዜ እንደምታሳየው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስታነብ ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ እንዲሁም ማንኛውንም ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ነገር ማሳየት አለብህ ቤተ ክርስቲያን በታቅ አክብሮት ገብተህ በልብህ እንዲህ እያልክ ስትጸልይ «እኔ ግን በምህረትህ ብዛት ወደቤትህ እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስና መቅደስ እሰግዳለሁ::» ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነህ የእግዚአብሔርን መልአክና የማምለኪያ ቤት እንደሆነ ስሰማ ዳዊት ምን እንደአለ አስብ «አቤቱ እስከረጅም ዘመን ድረስ ለቤትህ ቅድስና ይገባል (መዝ. 93:5) ይህ ቤተ ክርስቲያንን መቅደሱን ጸሎቱን መፍራት ይሰጥሀል::

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማንም ጋር አታውራ ካወራህ ለቤተ ክርስቲያን እና ለጸሎት ያለህን ንቀት ያሳያል ወሬ ማውራትህና በጸሎት ውስጥ አለመሳተፍህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገባኸው እግዚብሔርን ባለመፍራት እንደሆነ ያሳያል::



አባታችን ያዕቆብ ያለውን አስታውስ «ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ እጅ ነው»:: (ዘፍ. 28:17) እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ አስፈሪ እንደሆነ ምንም አያጠራጥርም እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ የሚሰራበት ቦታ አስፈሪ ነው::

ለዚህ ነው ሙሴ እግዚአብሔር የሚናገርበት ቦታ ሲደርስ አምላክ እንዲህ ያለው «ወዲህ አትቅረብ አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ»:: (ዘፀ. 3:5) ይኸው ቃል ኢያሱ ተናግሮታል:: «አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ» (ኢያ. 5:15) ጫማን ማውለቅ በእግዚአብሔር ቤት ስትገኝ ቁሳዊ የሆነን ነገር የመጣልና የቅዱስ ቦታ አክብሮን የሚያሳይ ምልክት ነው::

በትንሹ በቤተ ክርስቲያን ስንቆምና ስንቀመጥ እግዚአብሔርን በመፍራት መሆን አለበት አጠገባችን ካለው ሰው ጋር ማውራት ወይም ስለምናስበው ስለምናየው ነገር አስተያየት መስጠት የለብንም:: ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር መፍራት በፍፁም በልቡ የለም:: ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ጋዜጣ በእጁ ይዞ የሚገባ ወይም በኪሱ ሲጋራ የያዘም ያው ነው:: የእግዚአብሔር ቤትን የማያከብር እግዚአብሔርን ራሱን አያከብርም እግዚአብሔርን የሚያከብር ግን ቤቱንም ያከብራል::

ይህ ፍርሃት መጽሐፍ ቅዱሳንም ሊያካትት ይገባል:: ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ሲነበብ ዲያቆኑ እንዲህ ይላል:: «እግዚአብሔር በመፍራት ቁሙ የእግዚአብሔርን ወንጌል ስሙ» ጉባኤው ሁሉ በአክብሮት በፍርሃት

www.ethiopianorthodox.org

ይነሣል:: ቄሱም በቃሉ በመገዛት ዘውዳቸውን ከእግዚአብሔር ፊት ያወልቃሉ::

ቄሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከማንበባቸው በፊት እንዲህ በማለት ይጸልያሉ:: «አምላክ ሆይ ቃልህን ለመስማትና ለመተግበር እንድንችል እርዳን»:: ከዚህም በኋላ ቄሱ እጣን እያጠኑ መጽሐፍ ቅዱሱን ይሰሙታል:: በዚህ መንገድ መጽሐፍ ቅዱሱን እናከብረዋለን? አንድ አንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በማንኛውም ቦታ ያስቀምጡና ከሌላ መጽሐፍ ጋር ሲጠፋ ይችላል::

እግዚብሔርን የሚፈራ መንፈሳዊ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ ቦታ ያስቀምጠዋል በላዩ ላይም ምንም ነገር አያስቀምጥበትም መስቀል ወይም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሊያስቀምጡበት ይችላሉ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን እናከብረዋለን:: እኛም ደግሞ በቤታችን መጽሐፍ ቅዱስን በአክብሮታዊ ፍርሃት እናነባለን:: እግዚአብሔርን መፍራት በውስጣችን ስላለ በውስጥ የተጻፈውን ትዕዛዝ እንፈራለን መጽሐፍ ቅዱሳን ማንበብና ሌላ መጽሐፍን ማንበብ ልዩነት እንዳለው ልታውቅ ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስን አልጋ ላይ ወይም ሻይ እየጠጣን ማንበብ የለብንም እንደዚህ ዓይነት ስህተቶች እግዚአብሔርን መፍራት ከልብህ ያርቁታል::

ቄሱ በጸሎቱ «መጽሐፍ ቅዱስን ለመስማትና ለመተግበር እርዳታ» ሲል መጽሐፍ ቅዱስን መስማት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጸሎትን ዕርዳታንና እጣን ማጠንን ይጠይቃል እስቲ ከዚህ ትምህርት እንውሰድ::

መለኮታዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያንን ስርዓት ስንካፈል እግዚአብሔርን መፍራት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ሰዎች በቴፕ



ወይም በቪዲዮ የተቀረፀ ስርዓት ሲሰሙ ይህንን ፍርሃት ያጡታል:: በሌላ ነገር ሲጠመዱ ወይም መኪና ሲነዱ ሲቀመጡና በትራፊክ ስርዓት ላይ ሲያተኩሩ ያጡታል:: በመኪናው ውስጥ የተቀረፀወ ስርዓቱን በመንፈሳዊ መዝሙር ፍፁም ስብከት ብንቀይረው ይሻላል::

ለመለኮታዊ የቤተ ክርስቲያን ስርዓት ያለንን ክብርን አክብሮታዊ ስርዓት ለመግለጽ አንድ ሰው በጥዋት መከታተልና ቄሱ ቡራኬ ቃለምዕዳን ሳይሰጡ ቤተ ክርስቲያን ለቆ መውጣት የለበትም:: ቤተ ክርስቲያንን ቤተ መቅደስን እና ቅዱስ ቁርባንን የሚያወድስ ማንኛውም ሰው በልቡ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት ሊኖር ይገባል:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ሰው በታላቅ አክብሮት መመልከት መቻል አለባቸው::

ስለዚህ ሰዎች በጠባቂያቸው መልአክ ፊት ኃጢአትን መስራትን ማፈርና የሚጠብቃቸውን መልአክ ማክበር አለባቸው:: መሰዊያውንና መስዋዕቱን እና የቤተ ክርስቲያንን መልእክት ማክበር አለባቸው:: ካህናት መንፈሳዊ አባቶች እና መንፈሳዊ መሪዎች በምድር ላይ ያሉ የእግዚአብሔር መጋቢዎች (ቲቶ. 1:7) እና የእግዚአብሔር ሚስጥር መጋቢዎች (1ቆሮ. 4:1) እንደሆኑ በማወቅ እያንዳንዱ ሰው ሊያከብራቸው ይገባል::

የቅዱሳን ምስል በብዙዎች ዘንድ የተከበረ ነው:: ቄስ በቅዱሳን ምስል ፊት እጣንን ያጥናል እኛ ደግሞ መንፈሳዊ ውዳሴና ዝማሬን ለመላእክትና ለቅዱሳን የምናዜም ከሆነ ታዲያ እነርሱን ለፈጠረውስ? የእግዚአብሔርን ሰው እንደምናከብር ሁሉ የእግዚአብሔርንም ቀን እናከብራለን:: የተቀደሰውን የእግዚአብሔር ቀን ማክበር የሚፈራ ሰው በልቡ ውስጥ እግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን መፍራት ሊኖር ይገባል:: ልክ እንደዚሁ ጾምን ማፍረስ የሚፈራ ሰው በልቡ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት አለ::

ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስለት የሚፈጽም ሰው እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ይደርሳል:: ስለት በእግዚአ ብሔርና በሰው መካከል የሚፈፀም ስምምነት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለውም በፍርሃትና በአክብሮት መፈፀም አለበት:: «ተስለህ የማትፈፅም ብትሆን ባትሳል ይሻላል::» (መክ. 5:5)::

## እግዚአብሔርን ወደመፍራት ለመድረስ የሚሠሩ ልምምዶች

እግዚአብሔር ወደ መፍራት ለመድረስ የሚከተሉትን ነገሮች ተለማመድ:: ሁልጊዜ እግዚአብሔር ከፊትህ ይኑር ደግሞም ስራዎችህ በሙሉ በእርሱ ፊት የተገለጡ እንደሆኑ አስታውስ:: ሁሉንም ስራችሁን ይመለታል ንግግራችሁንም ይሰማል:: ቅዱስ መቃርዮስ እንዲህ አለ:: «የምንሰራው ማንኛ ውም ነገር በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ ነው:: ከእርሱ የተደ በቀ ምንም ነገር የለም::» (ሁል ጊዜ ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ በዚህ ቀን ስለሰራችሁት ነገር በሙሉ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠትን እንዳለባችሁ እወቁ:: ከዚያ በኋላ ኃጢአትን አትሰሩም እግዚአብሔርን መፍራትም በውስጣችሁ ይኖራል::) ብሏል ቅዱስ ኢሳይያስ::

የእኛ ችግር ኃጢአትን ስንሠራ እግዚአብሔርን ከፊታችን አለማስቀመጥ ነው:: ስለዚህ ኃጢአትን እንደ ውሃ እንጠጣለን እግዚአብሔርንም እንረሳለን:: ዳዊት በመዝሙሩ ላይ ስለ



ኃጢአተኞች «አቤቱ አመፀኞች በእኔ ላይ ተነስተዋል የክፉዎ ችም ማኀበር ነፍሴን ፈልጉአት በፊታቸውም አላደረጉህም::» (መዝ. 86:14) ያለው በከንቱ አይደለም:: ስለዚህ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ከፊታችሁ አድርጉ ከዚያ በኋላ ትፈራላችሁ ኃጢአትንም አትሰሩም::

«በፊቱ የቆምሁት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር» (1ነገ. 18:15) ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ቃል እንዴት አስደሳች ነው:: እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ለመድረስ ሁል ጊዜ ግር ማውንና ክብሩን ከፊታችሁ አስቀምጡ ከዛ በኋላ እግዚአብሔ ርን መፍራትን ታገኛላችሁ:: የነገሥታት ሁሉ ንጉሡ የጌቶች ሁሉ ጌታ የሆነው እግዚአብሔር (ራዕይ 19:16) የጌቶች ሁሉ ፈጣሪ ነው:: እኛ በእርሱ ፊት እንደ አቧራ ነን:: እንዴት ልንቃወመው እንችላለን?

ለእያንዳንዱ እንደሥራው የሚከፈልበትን የእግዚአብሔ ርን ፍርድ ከፊት አስቀምጡ (ማቴ. 16:27፣ ዮሐ ራዕ 22:12) «በኃጢአት ተይዤ ሳለሁ እንዴት ከእግዚአብሔር ፍርድ አመ ልጣለሁ? ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ::»

ኃጢአት የሚፀየፈውን የእግዚአብሔርን ቅድስና በፊታ ችሁ አስቀምጡ:: በጻድቃን ጓደኞቻችሁ ፊት ኃጢአት መሥራ ትን ወይም ክፉ ቃል መናገርን የምትፈሩ ከሆነ ይህንን ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት ለማድረግ እንዴት ትደፍራላችሁ:: ኃጢአት በቀጥታ እግዚአብሔርን በመቃወም የሚደረግ ነገር እንደሆነ አስታወስ:: «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደር ጋለሁ:: በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሰራለሁ?» (ዘፍ 39:9) ብሏል ዮሴፍ:: በኃጢአት በምትፈተኑበት ወቅት

www.ethiopianorthodox.org

ይህንን ጥቅስ ደጋግማችሁ አስተውሉት ከዚያ በኋላ እግዚአ ብሔርን መፍራት ወደልባችሁ ይገባል::

ኃጢአት በሠራችሁ ቁጥር የእግዚአብሔር መንፈስ ታሳ ዝናላችሁ (ኤፌ. 4:30) ከእርሱም ጋር ያላችሁን ህብረት ታጣላ ችሁ:: እግዚአብሔር በውስጣችሁ እንደሚኖር ቤተመቅደስ እራሳችሁን ውቀሱ:: «እራሴን ከኃጢአት ጋር ካስማማሁ እንዴት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ልሆን እችላለሁ? መንፈስ ቅዱስስ እንዴት በውስጤ ይኖራል?» ብላችሁ እራሳችሁን ጠይቁ:: «ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር ያፈርሰዋል የእግዚአብሐር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ:: (1ኛ ቆሮ 3:17)ብሏል ጳውሎስ::

ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስ ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላደርጋቸው አይገባም::» (1ቆሮ. 6:15) ብሎ ማለቱንም አስታውሱ:: የንስሐን ሕይወት የምትመራ ከሆነ እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ትደርሳለህ:: ንስሐ እግዚብሔርን ወደመፍራት ይመራሀል እግዚአብሔርን መፍራት ደግሞ ወደ ንስሐ ይመራ ሃል:: የንሰሐ ሕይወት የሚኖር ሰው ኃጢአት ምን ያህል አፀያፊ እንደሆነና ከእግዚአብሔር ለይቶ ለእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚያጋልጠው ስለሚያውቅ ይፈራል::

በንስሐ ጎዳና የሚጓዝ ሰው እንዳይወድቅ ይፈራል:: አንዴ ከወደቅኩ ወደ ክፉ ነገር ውስጥ እገባለሁ ብሎ ይፈራል:: ኃጢአት አስተሳሰቡን፣ ደርጊቱን እና ስሜቱን በሙሉ ተቆጣ ጥሮ ባሕሪው እንዳይሆንና እንዳይገዛው ስለሚፈራ «አሁን



ኃጢአትን መሥራት ከጀመርኩ ኃጢአት ሁለንተናዬን የሚገዛ በት ጊዜ ይመጣል» ብሎ ይናገራል::

ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራትን ሁልጊዜ እራሳችንን በመዳኘት ልናገኘው እንችላለን:፤ ሁል ጊዜ ጠዋት እና ማታ ምንስ እግዚብሔርን የሚያስደስት ነገር ሠራሁ? እያልን እራሳ ችንን መጠየቅ አለብን:: የንስሐን ሕይወት መምራት አለብን::

ሙሴ ፀሊም እንዲህ ብሏል:: «ጠዋት ከእንቅልፋችሁ ስትነሱ በዚህ ቀን ለምታደርጉት ለእያንዳንዱ ነገር ለእግዚአ ብሔር መልስ እንደምትሰጡ አስታውሱ::» ይህንን ፍርሃት ለማግኘት በየቀኑ እራሳችንን መፈተሽ አለብን:: እያንዳንዱ ሰው ግድየለሽ ወይም እግዚአብሔርን የማይፈራ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ልቡን መፈተሽ አለበት:: እግዚአብሔርን ወደ መፍራት በመመለስ ፍቅርን እስክናገኝ ድረስ ወደፊት እንጓዝ:: እግዚአብሔርን አለመፍራትን የሚያመለክቱ ምልክቶ ችን በማጤን እናስወግዳቸው::

ከኃጢአት ጋር የሚጓዝና የሚደራደር ሰው በልቡ ውስጥ እግዚብሔርን መፍራት የለም:: ክፉና ኩሩ የሆነ ሰው በልቡ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሌለ ግልፅ ነው:: ሌላው እግዚአብሔርን ወደ መፍራት ሊመራችሁ የሚችለው ነገር ሰዎችን እንደምትፈሩት እግዚአብሔርን መፍራት ነው::

በሰው ፊት ለማድረግ የምትፈሩትን ነገር በሙሉ በእግ ዚብሔርም ፊት ማድረግ ፍሩ:: ሰዎች እንዳያውቁባችሁ የማት ፈልጉትን ነገር በእግዚብሔር ፊት አታድርጉት:: እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ፍርድንም ይፈርዳል:: ሰዎች እንዳይሰሙት የምትፈሩትን ነገር በሙሉ እግዚአብሔር እንዳያየው ፍሩ::

www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች እንዳያዩት በመፍራት በድብቅ የምትፈጽሙትን ነገር በሙሉ እግዚአብሔር ፊት ለመፈጸም አትድፈሩ:: አለበለዚያ ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል:: «ለሰዎች የሰጣችሁትን አክብሮት ያህል ለእኔ አልሰጣችሁኝም አፈር ከሆነው ሰው ጋር እንኳን እኩል አልተመለከታችሁኝም::»

«ለዚህ አፈር ለሆነወ ሰው ክብርን ስትሰጡ ለእኔ ግን ምንም ዓይነት አክብሮት አላሳያችሁም. . .» በተዘጋው ክፍላ ችሁ ውስጥ እራሳችሁን እግዚአብሔርን መፍራትን አስለም ዱት:: ማንም በማይመለከታችሁ ጊዜ እግዚአብሔርን የምትፈሩ ከሆነ በይበልጥ ደግሞ ሰው በሚያያችሁ ወቅት እግዚብሔርን ትፈራላችሁ:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በድብቅ የሚሰራ ኃጢአትን ይጠነቀቃል::

ለምሳሌ አንዲት ሴት ማንም እርሷን በማያይበት ክፍሏ ውስጥ በስርአት የምትኖር ከሆነ ከቤቷ ውጪ በግድየለሽነት ሕይወቷን አትመራም:: ቤቷ ውስጥ ቁጭ ብላ ቀሚሷ ወደ ላይ ቢገለብ በፍጥነት ታስተካክለዋለች ምክንያቱም እግዚአ ብሔርን ትፈራለች:: በመላእክትና በቅዱሳን መንፈስ ፊት ሀፍረት ይሰማታል:: በሰዎች መካከል ስትሆን ይህንን ጨዋነቷን የምትተው ይመስላችኋል? በፍፁም ሊሆን አይችልም:: እግዚአ ብሔርን የሚፈራ ሰው ክፉ ሀሳብ ሲያስብ እንኳን ያፍራል::

እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ስለሚያውቅ የእግዚአ ብሔር ሀሳብን በሚቃወሙ የውስጥ ፍላጎቶች እና ዝንባሌዎቹ ሀፍረት ይሰማዋል:: መልካም ያልሆነ ሀሳብን ስታሰቡ እራሳችሁን ውቀሱት:: በሰዎች ላይ ከምትፈርዱት በላይ በራሳችሁ ላይ ፍረዱ::



በንስሀ አባታችሁ ፊት ንስሀችሁን ቀላል አታድርጉት:: ንስሀችሁን ተራ በሆነ መልኩ አታድርጉት:: ተረት እንደሚናገር ሰው ሳይሆን በሀፍረት፣ በመፀፀትና በሀዘን አድርጉት:: በቄሱ ፊት ለእግዚአብሔር እየተናዘዛችሁ እንደሆነ አስታውሱ:: በጣም በተፀፀታችሁና ባዘናችሁ ቁጥር እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ልባችሁ ዘልቆ ይገባል::

እግዚብሔርን ወደመፍራት ለመድረስ ከፈለጋችሁ በአለ ማዊ ምኞት የተያዛችሁ አትሁኑ:: ይህንን የማታደርጉ ከሆነ ስለሕይወታችሁና ስለ እጣ ፋንታችሁ ለማሰብ ጊዜ አይኖራ ችሁም:: እግዚአብሔርን ትዕዛዛቱን ትረሳላችሁ:: ከዚያ በመቀ ጠል በልባችሁና በሀሳባችሁ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት የሚባል ነገር አይኖርም::

ከጊዜ ወደ ጊዜ ይህንን ዓለም በመተው ሁልጊዜ እንተን ወደ ሚመለከተው እግዚአብሔር ተመልከቱ:: እግዚአብሔርን መፍራት ከፈለጋችሁ እግዚብሔርን ከሚፈሩ ሰዎች ጋር ህብረት አድርጉ::

ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ባህሪ እግዚአብሔርን መፍራትን ትማራላችሁ:፤ ልክ እንደነርሱ ጠንቃቃና ንቁ ትሆናላችሁ:: በሌላ በኩል ከክፉዎች ጋር ህብረት አታድርጉ:: ከልባችሁ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራትን አስወግዳችሁ ግድ የለሽ እንድትሆኑ ያበረታታቹሃል:: ከክፉዎች ህብረት እራሳችሁን አርቁ::

እግዚብሐርን ወደመፍራት ለመድረስ በእግዚአብሔር ላይ አታጉረምርሙ:: ለእያንዳንዱ ውድቀትና መከራ እግዚአ ብሔርን አትውቀሱ:: እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የሚወቅስ «እግ

www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ይህንን ነገር ለምን አደረገብኝ? ለምን ውድቀትንና መከራን አደረክብኝ? ለምን ታሰቃየኛለህ?» የሚል ሰው እግዚአ ብሔርን ከመፍራት የራቀ ነው::

ችግር ሲገጥምህ እግዚአብሔረን ሳይሆን እራስህን ውቀስ ከዛ በኋላ እግዚብሔርን ወደ መፍራት ትደርሳለህ:: እግዚአ ብሔርን ወደመፍራት ለመድረስ ከፈለክ የእግዚብሔርን ስም በታላቅ አክብሮት ካልሆነ በስተቀር በክንቱ አትጥራ:: (ዘፀ. 20:7)

የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ነውና ስሙን በከንቱ አት ጥራ:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ቅርርብ ለእግዚአብሔር ያለህን አክብሮት የሚያስጥልህ አይሁን:: በእያንዳንዱ ጸሎት ወቅት «ስምህ ይቀደስ» እንደምንል አትርሱ:: የእግዚአብሔርን ስም በአክብሮት በጠራን ቁጥር ፍርሃት በልባችን ውስጥ ስፍራን ይይዛል:: እስካሁን እግዚአብሔርን ወደመፍራት እንዴት መድ ረስ እንደምንችል ተናግሬያለሁ እስቲ አሁን ደግሞ እግዚአ ብሔርን በመፍራትና እግዚአብሔርን በመውደድ መካከል ስላለው ግንኙነት እንመልከት::



## ምዕራፍ ስድስት

# ፈሪሃ እግዚአብሔር ከፍቅሩ ይመጣል አብሮትም ይቀጥላል

ፈሪሀ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ምንነት ሳያውቁና በሁለቱ መካከል ያውን ግንኙነት ሳይረዱ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ወዲያ ብለው ፍቅሩን አጥብቀው ሊያዙ የሚ ሞክሩ ብዙዎች ናቸው:: ለእነዚህ ለእያንዳንዳቸው መናገር የምፈልገው ነገር አለ በእግዚአብሔር ፍቅር መኖር መልካም ነው ግን ያንን ፍቅር ለማግኘት እግዚአብሔርን በመፍራት መጀመር ይገባል:: የመንገድ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍ ራት ሲሆን መጨረሻው ደግሞ ፍቅሩ ነው:: መንገዱን ከመ ጨረሻው መጀመር አንችልም::

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአ ብሔርን መፍራት ነው» (ምሳ. 9:10፣ መዝ.111:10) ብሎ የሚገልፀውን የተፈጥሮ ትምህርት መቅሰም ይኖርብናል:: እግ ዚአብሔርን በመፍራት ውስጥ ትዕዛዛቱን መፈፀምን እንማራ ለን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ግን የመንገድ መጨረሻና የመንፈ ሳዊ ተግባር ሁሉ ጫፍ ነው::፤ «በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዛትህ ህጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል» (ማቴ 22:40) እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ሰው ሌላ ትዕዛዝ አያስፈልገውም ሌሎች መልካም ድርጊቶች ሁሉ በዚህ ስር ይጠቃለላሉና::

www.ethiopianorthodox.org

ብልህ ሰው መንገዱን ከመነሻው ይጀምራል፣ ይህም እግዚአብሔርን ከመፍራት ነው ይህ ፍርሀት ደግሞ በሂደት ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ይመራዋል:: እንዴት? አንድ ሰው ኃጢአትን እስካደረገ ወይም የኃጢአት ምኞት በልቡ እስካለ ድረስ በውስጡ ፈሪሀ እግዚአብሔር አይኖርም:: ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ከመፍራት መጀመር ይገባዋል ኃጢአትን የማ ድረግ ፍላጎት በውስጡ ቢኖር እንኳን ንስሐ ገብቶ ከኃጢአቱ መራቅ አለበት:: ብዙ ይፍጨረጨራል፣ ትዕዛዛቱን ለመፈጸም እራሱን እስከማስገደድም ይደርሳል:: ጸሎትን፣ ቃሉን ማንበብና ማሰላሰልን እንዲሁም ውዳሴን የመሳሰሉትን የፀጋ መንገዶች ይከተላል:: ገና የእግዚአብሔርን ፍቅር ያልተለማመደ ቢሆን አንኳን እነኚህን ነገሮች ያደርጋቸዋል፣ ለመታዘዝ ሲል ብቻ ይህ ሰው ያለበት ደረጃ «ስጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ይመኛል፣ እነዚህ እርስ በእርሳቸው ይቃወማሉ» (ገላ. 5:17) ተብሎ የሚገለፅ ነው::

የመንፈሳዊው መንገድ ጀማሪ ገና ከኃጢአት ነፃነትን አልተቀዳጀም ስለዚህ እራሱን ከኃጢአት ያርቃል:: ይህን የሚ ያደርገው የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝንና እንዳያስቆጣ የቅጣቱም ተካፋይ እንዳይሆን ነው::

ሁኔታዎች ግን እንደነበሩ አይቀጥሉም:: ትዕዛዛቱን በፈፀመ ቁጥር በእነርሱ መደሰትና መውደድን ይጀምራል:: «ምስክሮችህ ድንቆች ናቸው» (መዝ. 119:129)፤ ብሎ ያምንና ብዙ ሽልማትን እንዳገኘ ሰው ሀሴት ያደርጋል፣ መልካም ማድረግንም ይወዳል:: ቀምሶ ወደወደዳቸው ንፅህና፣ ቅድስናና መንፈሳዊነት የመራውን ትዕዛዝም ያፈቅራል:: እግዚአብሔርን



በመፍራት ሳንኖር ፍቅሩን ልናገኝ እንችላለን ብለን ማሰብ ፍፁም ስህተት ነው:: ፈሪሀ እግዚአብሔር ብቻ ነው ልብን አንፅቶ የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ እንዲሆን ሊያበቃው የሚችል:: መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በልባችን የእግዚአብሔርን ፍቅር ያፈሳል:: በዚህ መንገድ ነው እንግዲህ ሰው ከፈሪሀ እግዚአብሔር ወደ ፍቅሩ መሸጋገር የሚችለው::

ይህ ሽግግር ግን በአንዴ የሚሆን አይደለም:: ከብዙ ትግልና የፀጋ ተግባር በኋላ የሚደረስበት ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ባለ ትግልና ጥረት ውስጥ ነው ስራ ቁርጠኝነቱንና ልፋቱን ለእግዚአብሔር የሚያረጋግጠው:: እግዚአብሔርም ውሳኔውን ሲያይ ፍቅሩን በልቡ ከማፍሰስም አልፎ ኃጢያት በውስጡ ከፈጠረው ግጭት ያፅናናዋል:: ከመውደቅ ፍርሀትም ያበረታዋል::

ምንም እንኳን ይህ መንገድ ግልፅ ቢሆንም አንዳንዶች ቅዱስ ዮሐንስ በ(1ዮሐ. 4:18) ላይ «ፍፁም ፍቅር ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሀት የለም....» ብሎ የገለ ፀውን በተሳሳተ መልኩ ይተረጉሙታል:: ይህን ክፍል እንመረ ምርና ስለየትኛው ፍርሀት እንደሚገልፅ ፈሪሀ እግዚአብሔር የመንገድ መጀመሪያ ከመሆኑ ጋርም ይጋጭ እንደሆን እንይ:: ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ ክፍል ፍርሀት ሲል ሊገልፅ የፈለገው በፍርድ ቀን የሚኖረውን ከፍተኛ ሽብር ሊሆን፤ ይችላል:: ወዲያው ቀጥሎ ፍርሀት ቅጣት አለውና ማለቱ ለዚህ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: ቅዱስ ጳውሎም «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው» (ዕብ 10:31) ይላል::

www.ethiopianorthodox.org

ወደዚህ ፍርሀትን አውጥቶ ወደሚጥል ፍፁም ፍቅር ማን ደረሰ? ፍፁም ፍቅርስ ምንድን ነው? ብለን እንጠይቅ:: ሰው እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ከፍቅሩ በጣም ሊርቅ ይችላል:: ለፍቅሩ፣ እውነተኛ (ዮሐ. 15:10) እዲሁም «ትዕዛዙ በእርሱ ዘንድ ያለች የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው» (ዮሐ. 14:21) ብሎ ይናገራል:: በዚህ መሠረት እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያሉ ትዕዛዛቱን መተላለፍ የሚቻል አይደለም:: ቅዱስ ዮሐንስ በተጨማሪም ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአ ብሔር ፍቅር ይህ ነውና...» ብሎ ይጽፋል:: ቃሉን ግን የሚ ጠብቅ ሁሉ በእርሱ «የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈፅሞ አል::» (1ዮሐ 2፤4-5):: ስለዚህ ከሁሉ አስቀድመን ትዕዛዛቱን መጠበቅ የሚገፋፋን ፈሪሀ እግዚአብሔርን ልንይዝ ይገባል:: በኃጢአት እየኖርንና የእግዚአብሔርን መንፈስ እያሳዘንን (ኤፌ 4:30) እራሳችንን በማታለል የእግዚአብሔር ፍቅር አወርስሀለሁ ልንል አንችልም::

ኃጢአትን የሚያደርግ ማንኛውም ሰው የፍቅርም ሆነ የፍርሀት ደረጃ ላይ አልደረሰም፣ ገና መንፈሳዊውን ጉዞ አልጀ መረም:: እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ እስከኖረ ድረስ፣ አይወደ ውምም አይፈራውምም ከብርሃን ርቆ ገና በጨለማ ነው ያለው:: ቅዱስ ዮሐንስ በግልፅ እንደሚያስቀምጠው «ከእርሱ ጋር ህብረት አለን ስንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም» (1ዮሐ 1:6):: በጨለማ መመላለስ ደግሞ ፍርሀት እንዳለበት እርግጥ ነው::

እንግዲህ እግዚአብሔርን መውደድ ትዕዛዛቱን መፈጸም ከሆነ፣ ፍርሀትን አውጥቶ የሚጥል ፍጹም ፍቅር ምንድን ነው?



ወደ ፍፁም ፍቅር የሚደርስ ሰው ልቡ ሁሌም በእግዚአ ብሔር ፍቅር የተያዘ ነው:: የኔ ፍቅር ማንኛውንም የኃጢአት ፍላጎት ያጠፋዋል ወይም «...ኃጢአት ሊያደርግ አይችልም::» (1ዮሐ. 3:9) በመልካም ጎኑ የእግዚአብሔር ፍቅር ሙሉ ሕይ ወቱን፣ ልቡን፣ ሀሳቡንና ጊዜውን ሲቆጣጠር እናየዋለን:: እግዚ አብሔርን በፍፁም ልቡ፣ በፍፁም ሀሳቡ፣ በፍፁም ነፍሱና በፍ ፁም ኃይሉ ይወደዋል:: (ዘዳ 6:5፣ ማቴ 22:37):: በቀንና በሌ ሊት ስለእግዚአብሔር ያሰላስላል:: ይህ የፍፁም ፍቅር አንድ ከፍታ ነው ወደ እግዚአብሔር የደረሰ ሰው ፍርሀት በውስጡ የለም::

ማንም ሰው «ልጆቼ ሆይ እኔ እግዚአብሔርን አልፈ ራም» ብሎ ለተከታዮቹ የተናገረውን የቅዱስ አንቶኒንን ንግግር መድገም የለበትም:: ተከታዮቹም የተናገርከው ከባድ ንግግር ነው:: ባሉት ጊዜ የመለሰላቸው «ይህን ያልኩት ስለምወደው ነው፣ ፍቅር ፍርሀት አውጥቶ ይጥላል» ብሎ ነበር:: እዚህ ጋር ማንኛችን ነን ይህንን ቅዱስ አንቶኒ የደረሰበት የእግዚአብሔር ፍቅር ደረጃ ላይ የደረስነው ብለን መጠየቅ አለብን:: እነዚያ ታላላቅ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ከፍ ያለና የጠበቀ ግንኙነት መስርተዋል:: ልባቸው ከሌላ ነገር ሁሉ በማፅዳታቸው በልባቸው የሚቀረው እግዚብሔር ብቻ ነው::

ቅዱሳን የደረሱበትን ከፍተኛ ደረጃ እንዳገኘን በሀሰት እንናገራለን? እነሱ የደረሱበት ላይ ሳንደርስ ንግግራቸውን ብቻ እንደግማለን:: የእግዚብሔር ፍቅር የስጋን ምኞትና የልብን ቁሳዊነት አውጥቶ ከልባችን የጣለበት ደረጃ ላይ ደርሰናል? ከክርስቶስ ፍቅር ጋር ስናስተያያቸው ሌሎች ተወዳዳሪ ፍቅሮችን

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ እንደቆሻሻ ቆጥረን ከልባችን አውጥተናል? ቅዱስ አውግስ ቲኖስ ሲናገር «በምድር ምንም እንደማልፈልግ ምንም እንደ ማልፈራ ሲሰማኝ የምድር አፈር ላይ ተቀመጥኩ» በልባችን እስካሁን የዓለም ፍቅርና ምኞቱ ከኖሩ፣ ፍርሀትን አውጥቶ የሚጥለውን ፍጹም የእግዚአብሔር ፍቅር ገና አልተለ ማመድንም::

እንዲሁም ሆኖ ቅዱስ አንቶኒ ስለፈሪሀ እግዚአብሔር ይናገራል፤ እንዲህ ይላል:: «ብርሃን ወደጨለማ ቦታ ሲገባ እንደሚያበራው ፈሪሀ እግዚአብሔርም ወደሰው ልብ ሲገባ አለማወቅን አስወግዶ ጥበብን ያስተምራል:: የትም ስትሄድ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር በዓይናችሁ ፊት ይሁን፣ ምንም ስታደርጉ፣ ከመንፈሳዊ መጽሐፎች ማረጋገጫን አግኙ» ቅዱስ አንቶኒ ተከታዮቹን እግዚአብሔርን መፍራትን ያስተማራቸው እንዲህ ነበር::

እግዲህ ፍርሀትን አውጥቶ ወደሚጥለው ፍፁም ፍቅር ደርሰናል አትበሉ ይልቅስ አምላኬ ሆይ ልወድህ እፈልጋለሁ ግን ወዳዚህ ፍፁም ፍቅር ገና አልደረስኩም:: እባክህ አንተው ሰጠኝ እኔ በፍርሀት እመላለሳሁ አንተ እባክህ ፍቅርህን ስጠኝ ብንል የተሸለ ይሆናል::

ጌታችን ሲናገር በጥቂቱ ታምነሀልና በብዙ እሾምሀለሁ (ማቴ. 25:21) ይላል:: በጥቂቱ ታማኝ መሆን ማለት ፈሪሀ እግዚአብሔር ነው ብዙ በሆነው ፍቅሩ ላይ እንድንሾም እን ጸልይ:: እግዚአብሔርን በመፍራት ብንኖርና ትዕዛዛቱንም ባን ተላለፍ ፍቅሩን ያስተምረና በመንፈስ ቅዱስ በኩልም በልባችን ያፈስዋል::



## ፈሪሃ እግዚአብሐርም ቢሆን ያለእናንተ መገኘት አይችልም

«. . .ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም. . .» (ዮሐ 15:5) ያልከው አንተ አይደለህምን? ያለእርሱ ምንም ልናደርግ አንችልም:: ስለዚህ እንዲህ ብለን እንጸልይ:: «ጌታ ሆይ መንገዱን ካንተ ጋር እንድጀምር እርዳኝ:: የአንተን ምሪትን እንዳገኝ እርዳኝ ያኔ በመታዘዝ እኖራለሁ:: በመታዘዝና አንተን በመፍራት ታማኝ እሆናለሁ አንተ ደግሞ ነፃ ስጦታ የሆነውን ፍቅርህን ትሰጠኛለህ:: ፈሪሀ እግዚአብሔር ፍቅር የሚመሰረ ትበት ጠንካራ መሰረት ነው:: ከመውደቅ የሚጠብቅህ ይህ ፈሪሀ እግዚአብሔር ነው::

ጌታ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መልአክ ሲናገር «ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፣ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሀልና» ይላል (ራዕይ 2:4) ሐዋርያው ጳውሎስም ስለገላትያ ሰዎች ሲናገር በመንፈስ ጀምረው በስጋ እንደጨረሱ ይገልጻል:: (ገላ 3:3) ለምንድ ነው በስጋ ሊቀጥሉ የቻሉት? ፈሪሀ እግዚአብሔር ስለዚህ ከመውደቅ የሚጠብቅ ጠንካራ አለት ነው:: ለዚህ ነው የኤፌሶን መልአክ የቀደመ ፍቅሩን ሲተው ጌታ በፈሪሀ እግዚአ ብሔር ያስተማረው:: እንዲህ ሲል ነው «አለዚያ እመጣብሀለሁ ንስሀም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ» (ራዕ 2:5) ፍቅር ዋነኛ ነገር ነው፣ በኃጢአት ሊጠፋ በፈሪሀ እግዚአብሔር ደግሞ ሊገኝ ይችላል::

ስለዚህ መከላከያም መድኃኒትም ነው:: መከላከያነቱ ኃጢአት ከመፈፀም ይከላከለናል:: የኃጢአት ፍላጎታችን ከፈሪሀ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ከበለጠ እንወድቃለን ከእግዚአብሔር ፍቅርም እንርቃለን:: እግዚአብሔር ግን ዳግመኛ መጥቶ ከወደቅንበት በንስሀ ያነሳናል:: ይኸው ፍርሀት ከእግዚብሔር ጋር ታርቀን ወደፍቅሩ ለመመለስ እንሞክራለን:: አሁን አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ይቀራል:: «የእግዚአብሔርን ፍቅር ካገኘን ከፈሪሀ እግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ጨርሶ ይቋረጣል? አይቋረጥም . . . ግን እንዴት?



## ምዕራፍ ሰባት

## ፍቅርና ፍርሃት

### በታላቅ የአክብሮት ስሜት እግዚአብሔርን መፍራት

ቅዱስ ማርይስሐቅ እንዲህ አለ:- «እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን ከመውደድ ይቀድማል::» እንዲህም ብሏል «እርሱን መፍራት እርሱን ወደመውደድ የሚመራን መንገድ ነው::» ያለጀልባ ወንዝን መሻገር እንደማንችል ሁሉ ንስሐ ሳንገባና እግዚአብሔርን ሳንፈራ ወደ እርሱ ፍቅር መድረስ አንችልም:: ንስሐ ጀልባው ነው፣ ፍርሃት መቅዘፊያው ነው፣ ፍቅር ደግሞ የሰላምና የክብር መጠለያ ነው:: እግዚአብሔርን መፍራት ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ይመራል ደግሞ ፈፅሞ የማይነጣጠሉ ናቸው::

ፍቅር እግዚአብሔርን ከመፍራት ከፍ ያለ ነገር ነው:: ነገር ግን ፍቅር ፈፅሞ ፍርሃትን አይቃወምም:: ፍቅር በደረጃው ከፍ ያለ ነገር ነው:: ቢሆንም ግን ልክ እንደመሰላል ወይም ከሀይስኩል ወይም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርቱ ይልቅ በትምህርቱ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ እንደደረሰ የኮሌጅ ተማሪ ከስሩ ያለውን ነገር አያጣም ይልቁንም ይደገፋቸዋል:: ያለፈባቸውን ነገሮች በፍፁም አይረሳቸውምም አይጠላቸውምም:: አሁን የተሻለ ነገር እያገኘ ነው:: ነገር ግን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱ ከኮሌጅ ትምህርቱ ጋር አይጋጭም::

www.ethiopianorthodox.org

ፍርሃት ወደ ፍቅር ይመራል ከዛ ፍቅርን ይጋርደዋል (ይጠብቀዋል)። ፍቅር በውስጡ ፍርሃትን ይጠብቀዋል።

በፍቅራቸው ፍርሃት የጣሉ ሰዎች ልክ ፍቅር በነበራት፣ ለጌታ ስትል በምትተጋው እና በማትሰለቸው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደሆነው የቀደመው ፍቅራቸውን ሲጥሉ፣ ሲወድቁና ንስሀ መግባት ሲያስፈልጋቸው ይችላል። ወደ እንከን የለሽ ፍቅር የደረሱ ሰዎች በርካታ እግዚአብሔርን የመፍራት ባህሪያትን ይይዛሉ። ምንድን ናቸው? ጥንቃቄ፣ ዝግጁነትና አስተዋይነት ናቸው። በሕይወቱ ውስጥ እግዚአብሔርን በመፍ ራት ለእነዚህ ነገሮች የተሰጠ ነው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመጠበቅ ይተጋል። በእንባና በመፀፀት የታጀበን የንስሐ ሕይወት ይመራል። አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወቅት በዚህ መልኩ ካልተጓዘ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መን ገድ አጥቷል። በእርሱ ፍርሃት ውስጥ ሳያልፍ ወደ እግዚአ ብሔር ፍቅር መዝለል የሚፈልግ ሰው ሲበከልና ግድ የለሽ ሊሆን ይችላል።

ቅዱስ አንቶኒ ለደቀመዛሙርቱ «እግዚአብሔርን አልፈ ራም» ብሎ ሲነግራቸው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ያገኘው ነገር ነው እንጂ የጀመረበት ነገር አይደለም። የጀመረው እግዚአብሔርን በመፍራት ነበር። የሙት አባቱን ሬሳ ካየ በኋላ «አንተ ያለ ፍቃድህ ይህንን ዓለም ተለይተሃል እኔ ግን ይህንን ዓለም እንድለይ ከመገደዴ በፊት በእራሴ ፈቃድ እለያሁ። አለው። ፍርሃት ልክ ከፍ ብሎ እንደሚያድግና ፍሬያማ እንደሚሆን የዛፉ ስር ነው። ምንም እንኳን የተደበቀ ቢሆንም ለዛፍ በጣም አስፈላጊ ነው አለበለዚያ ግን ዛፉ ይሞታል።



«እንከን የለሽ ፍቅር ፍርሃትን ያስወግዳል» ማለት ስጋትን ያስወግዳል ማለት ነው። የእሳትና የዲኑ ባህር ስጋት (ራዕይ 20:10) «ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» (ማቴ 13:42) ስለዚህ አስፈሪው ሁኔታው «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ ነው።» (ዕብ 10:31) እያለ ቅዱስ ጳውሎስ ይናገራል። እንከን የለሽ ፍቅር ላይ የደረሰ ሰው ከእግዚአብሔር እለያለሁ ወደ ጨለማም እጣላለሁ ብሎ አይሰጋም። ነገር ግን ልቡ በአክብሮት ስሜት እግዚአብሔርን በመፍራት የተሞላች ናት።

ነቢዩ ሙሴ እግዚአብሐርን «ከመአትህ ተመለስ ለህዝ ብህም በክፋታቸው ላይ ራራ።» (ዘፀ. 32:12) ብሎ እንዲናገር የሚስችለው ቅርርብ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረው። ነገር ግን አስርቱን ትዕዛዛት ለመቀበል ወደ ተራራው ላይ በወጣ ጊዜ «እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ...» (ዕብ 12:21) አለ። ይህ ምን ያህል እግዚአብሔር አስፈሪ እንደሆነ ያሳያል።

## እግዚአብሔርን የማሞገስ ትርጉሙ ምንድን ነው?

እግዚአብሔርን ማሞገስ እግዚአብሔርን የማክበርና የመ ፍራት አይነት አይደለመን? በዮሐንስ ራእይ መልእክቶቹ «ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና የፅድቅህም ሥራህ ስለተገለጠ አህዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ።» (ራዕይ 15:4) ይላሉ። ቅዱስ ዮሐንስ ዘላለማዊ ወንጌልን ለአህዛብ ሁሉ ይዞ» . . .እግዚአብሔርን

www.ethiopianorthodox.org

ፍሩ ክብርንም ስጡት ...» (ራእይ 14:7) እያለ ከሰማይ መካከል የሚበር መልአክ አየ:: እዚህ ጋር እግዚአብሔርን መፍራት እራሱን ከማክበር ጋር ይዛመዳል::

እግዚአብሔር እራሱ ይህንን ነገር ይፈልጋል:: ስለዚህ ለእርሱ ያንን ክብር አንረሳም በአርሱም ላይ ኃጢአትን አንሰራም:: መልአኩ ለሙሴ በሚነደው ቁጣቁጦ በተገለጠበት ጊዜ «አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ» (ዘፀ 3:5) አለው:: ይህ እግዚአብሔርን የመፍራት ምሳሌ አይደለምን? ሌላው ምሳሌ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራትና ትዕዛዙን በመጣስ የሚመጣው ቅጣት ነው:: (ዘፀ 20:7)::

ይህ ከአስርቱ ትዕዛዛት መካከል አንዱ ነው:: በአዲስ ኪዳን ላይ በተራራው ስብከት ላይ ተመሳሳይ ትዕዛዝ እናገኛለን:: የጌታ ስም የተመለከተ ብቻ ሳይሆን እርሱን ለሚመለከት ነገር ሁሉ ነው ትዕዛዙ:: ‹‹እኔ ግን እላችኋለው ፈፅማችሁ አትማሉ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቋ ንጉስ ከተማ ናትና...›› (ማቴ 5:34-35)

ለእግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ለተገናኘ ነገር በሙሉ አክብሮት ነው:: በልቡ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት ያለው ሰው እግዚአብሔርንና ለእርሱ የቆመውን ነገር በሙሉ ይፈፅማል:: ያከብራል ደግሞም ትዕዛዙን ይጠብቃል:: ቅዱስ ቦታችን፣ መጽሐፍን፣ ቅዱሳንና መላእክትንም ያከብራል:: ቅዱስ



ስሙንም ያከብራል በከንቱም አይጠራውም:: ነገር ግን ስሙን ያከብራል ስሙን በሚጠራበትም ጊዜ ይሰግዳል:: ይህ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው በሙሉ የሚኖረው እግዚአብሔርን በመፍራት ነው::

በዚህ ፍርሀት ቅጣቱን ይፈራልና ትዕዛዙን አይጥስም:: በፍቅሩ በኩል ደግሞ ትዕዛዛቱን ስለሚወድና በእነርሱ ደስታን ስለሚያገኝ ትዕዛዛቱን አይተላለፍም:: የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጥስ ሰው እግዚአብሔርን ከመፍራትና ከእርሱ ፍቅር የራቀ ነው::

ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እያወራ ትዕዛዙን የሚተላለፍ ሰው በእርግጠኝነት በከንቱ እያወራ ነው:: የመንፈሳዊው ጎዳና መጀመሪያ የሆነውን እግዚአብሔርን መፍራት ላይ ያልደረሰ ሰው እንዴት የመንፈሳዊው ጎዳና መጨረሻ ስለሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ሊያወራ ይችላል? «ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ ከፈረሶች ጋሪ መታገል እዴት ትችላለህ? (ኤር 12:5) የሚሉት ቃላት ምን ያህል አስደሳች ናቸው::

አንድ ጊዜ በመውደቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመነሳት ከኃጢአት ጋር እስካሁን የምትታገሉ ሰዎች ከሆናችሁ የታዘዙትን ሁሉ ከፈፀሙና ነገር ግን ስለራሳቸው «... የማንጠቅም ባሪያዎች ነን» (ሉቃ. 17:10) ከሚሉ ሰዎች ጋር እንዴት ራሳችሁን አብራችሁ ትመድባላችሁ? እንዴት ራሳችሁን ከቅዱሳንና ራዕይ ካላቸው ሌሎች ቅዱሳን ጋር ታወዳድራላችሁ::

www.ethiopianorthodox.org

እስቲ አሁን ስለደረጃችን እናውራ:: ከፍተኛ ደረጃን ሳናገኝ እንዳገኘን አድርገን እናውራ:: መልእክት እያስተላለፍኩ ያለሁት እንደኔ ላሉ ሰዎች ነው:: ሁላችንም ግባችን ላይ ለመ ድረስ እንታገላለን ነገር ግን እስካሁን አልደረስንም:: እስካሁን በትግል ደረጃ ላይ ነው ያለነው:: ይህ ሁላችንም የምንገኝበት ሁኔታ ነው:: ፍርሃትን የሚያስወግደው እንከን የለሽ ፍቅር መላው ሕይወታችንን ይፈልጋል::

ኃጢአትና ፍርሃት የሌለበት ዘላለማዊው ሕይወት እስኪ መጣ ድረስ ምንም ሰው ወደ እንከን የለሽ ፍቅር የሚደርስ አይመስለኝም:: በዚህ ምድር ላይ ኃጢአት ባለበት ቦታ ፍርሃት ሊኖር ይገባል ምክንያቱም ፍርሃት ኃጢአትን ይከተላል:: «ባለሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ .... ክፉ ብታደርግ ፍራ. . .» (ሮሜ 13:3-4) ይላል መጽሐፍ ቅዱስ:: ይህ ክፉውን ለመፈተን የተወሰነ ስልጣን ስላለው ሰው ከተጻፈ በቅድስው ውስንነት ስለሌለበት እግዚብሔርስ?



ምዕራፍ ስምንት

# ተቃውሞና ማስተባበል

የፀጋ ኪዳን ከሆነው አዲስ ኪዳን ጋር ይጋጫል በሚል ግምት «እግዚአብሔርን መፍራት» የሚለውን ሀሳብ መሸሽ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ:: የሚከተሉትን ሀሳቦችም እንደ መረጃ ያቀርባሉ::

1. እግዚአብሔር አመንዝራና ወርበላ የነበረውን ቅዱስ አውግስቲንን ከተቀበለው ታዲያ ለምን እግዚአ ብሔርን እንፈራዋለን ይላሉ::

ደግሞም እግዚአብሔር ነፍሰ ገዳዩን ሙሴ ጸሊምን፣ በአመንዝራነት የኖረችውን ግብፃዊቷን ማርያም፣ ሰባት አጋንንት ያወጣላትን መግደላዊት ማርያምን (ማር. 16:9) እና በፈሪሳው ያን ቤት ያገኘችውን አመንዝራዋን ሴት (ሉቃ.7:37) ተቀብሏል::

ልጄ ሆይ እነዚህን በሙሉ ማወቅ በረከት ነው:: ነገር ግን ከአንተ ጋር ስወያይ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እወዳለው:: «ከእነዚህ ቅዱሳን እንደ አንዱ እውነተኛ ነስሐ ገብተህ ታውቃለህ?» ደግሞም ወደ ኃጢአት እንዳልተመለሱት እና በቀረው ዘመናቸው ለብዙዎች ምሳሌ እስኪሆኑ ድረስ በመንፈ ሳዊው ሕይወታቸው በማደግ እንደቀጠሉት አውገስቲንና ሙሴ ፀሊም ንስሐ ገብታችሁ ታውቃላችሁ?

www.ethiopianorthodox.org

እራሷን እንዳዋረደችውና እንባዋን በሰው ሁሉ ፊት እንዳፈሰሰችው አመንዝራ ሴት የሚፀፀት ልብ አላችሁ? የግብጿን ቅድስት ማርያም እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ በፍርሃት ውስጥ እንደመራት ታውቃላችሁ? እጇ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳትገባ አደረጋት ደግሞም አንድ ቦታ ቀጥ ብላ እንድትቀር አደረጋት:: ስለዚህ ወደ ቅዱስ የፃድቃን ምስል መድረስ አትችልም:: ንስሐ ከገባች በኋላ እንዴት አድርጋ የሰይጣን ተደጋጋሚ ብልጠት በመቋቋም ለአስራ ሰባት ዓመት እንደቆየች ታውቃላችሁ?

ፍርሃትን ሊያስወግድ የሚችል ጠንካራ ፍቅር እንደነበራት መግደላዊት ማርያም በልባችሁ ውስጥ ፍቅር አለ? የእነርሱን የፍቅርና የንስሐ ምሳሌ ተከተሉ ከዛ በኋላ አትፈሩም:: ይህንን መረጃ መቼና እንዴት እንዳገኙትም አሰላስሉ::

ነገር ግን እናንተ የቅዱሳን ደረጃ ላይ እንደደረሳችሁ አታሰቡ:: የናንተ ነገር ከእነርሱ ይለያል ደግሞም የናንተ ንስሐ እንደ እነርሱ አይነት ንስሐ አይደለም:: በእናንተና በእነርሱ መካከል እና በእናንተ መጀመሪያና በእነርሱ መጨረሻ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ:: ነገር ግን በእናንተ ልብ ውስጥ ተስፋን እንዲያሳድሩ ሁል ጊዜ አስቧቸው:: በተመሳሳይ ቆራጥነት፣ ትጉህነትና እነርሱ በጀመሩበት አይነት ፍርሃት የእነርሱን መንገድ ለመከተል የሚቻላችሁን ሁሉ ሞክሩ::

ብዙ ስለወደደች ብዙ ይቅር ብያታለው ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አመንዝራዋ ሴት የተናገረውን አስታውሱ:: ይህንን ያህል ፍቅር፣ እፍረት እና እምባ ካገኛችሁ ወደ



ፍቅር የሚወስደውን ፍርሃት ታገኙላችሁ:: መለኮታዊውን ተስፋ ትቀበላላችሁ ደግሞም አትፈሩም::

2 «በጣም ርህሩህ አባታችን ሆኖ ሳላ ለምን እግዚአብሔርን እንፈራዋለን?» ስትሉ እሰማችኋለው::

አባትነት የሚጠይቀውን በሙሉ የሟላ አባት ነው:: መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ላይ ስለ እግዚአብሔር «እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም አንደ በደላችንም አልከፈለንም ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምህረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ:: (መዝ. 102:10-11) ይላል::

ልጄ ሆይ በዚህ መዝሙር ላይ በተለይም በዚህ ጥቅስ ላይ ማተኮርህ መልካም ነው:: እስቲ አንድ ላይ እናንብበውና ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት:: «አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል» (መዝ. 102:13) ይላል መዝሙረኛው:: ዳዊት እርሱን ለሚፈሩት እግዚአብሔር ይራራል ነው እንጂ ያው ትዕዛዙን ለሚጥሱና ኃጢአትን በመሥራት ለሚቀጥሉ ይራራል አላለም:: (መዝ 102:13) ስለ እግዚአብሔር መሀሪነት ይቅር ባይነት «ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምህረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ::» (መዝ 103:11) ይላል::

ከአንተ አስተሳሰብ ጋር የሚስማማውን ጥቅስ ብቻ ወስደህ የቀረውን ተውከው እግዚአብሔር ህዝቡን እዴት አድርጎ እንደሚይዝ ለማወቅ (መዝ 103) በሙሉ ማንበብ ሲገባ ቁጥር አስርንና አስራሁለትን ብቻ አይተህ ቁጥር አስራ አንድንና አስራ ሦስትን ግን ተውከው::

www.ethiopianorthodox.org

በትክክልም እግዚአብሔር፣በጣምርህሩና ታጋሽ አምላክ ነው፡፤ ነገር ግን በዚህ መሠረት ሁላችንም ንስሐ መግባት አለ ብን:: እግዚአብሔርን በመፍራታቸው ንስሐ ገብተው ኃጢአታ ቸው ስለተሰረየላቸው እርሱን ለሚፈሩት ይራራላቸዋል እንደ ኃጢአታቸውም አያደርግባቸውም:: ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ተናዘዙት ኃጢአታቸው ይቅር እንደተባለው በደላቸው አይፈር ድባቸውም:: እግዚአብሔር አንተን እንደ አባት ይገናኝሀል አንተ ደግሞ እርሱን እንደ ልጅ ልትገናኘው ይገባል::

በእርግጥም እግዚአብሔር አባታችን ነው ደግሞም አያዳ ላም:: ይህን በተመለከተ ቅዱስ ጴጥሮስ «ለሰው ፊትም ሳያዳለ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ::» (1ኛ ጴጥ. 1:17) ይላል::

ከቃሉ እንደምንረዳው አባት ነው:: ነገር ግን ኃጢአትን የማይታገስ ቅዱስ አምላክ ነው:: በልጆቹ መካከል አድሎን የማያደርግ ፍፁም አባት ነው ያለምንም ማዳላት እንደበደላችን ስለሚፈርድብን ፍቅሩንም እንዳናጣ ከኃጢአት እንገለል:: እግዚ አብሔር አባታችን ነው እንደ አባት ደግሞ ልጆቹ ሳይታዘዙ ሲቀሩ ይወቅሳቸዋል ነብዩ ኢሳይያስ ትንቢቱን «እግዚአብሔር ተናግሯልና ሰማያት ስሙ ምድርም አድምጪ ልጆችን ወለድሁ አሳደግሁም እነርሱም አመፁብኝ::» (ኢሳ. 1:2) በማለት ይጀ መራል:: እግዚአብሔርም ደግሞ በነብዩ ሚልክያስ በኩል «ልጅ አባቱን ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፍራቴ ወዴት አለ?» (ሚል 1:6) ብሏል:: የእግዚአብሔርን ክብር መቃወም ከእግዚአብሔር ቃል



ጋር የሚጋጭና በልባችን ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሌለ የሚያሳይ ነው ብለን ማለት የለብንም? የእግዚአ ብሔር ልጅ ከሆንክ እንደ አባትነቱ የሚገባው ክብር የት አለ?

**3** አንዳንድ ሰዎች «አባትነቱ ከመልካምነት እና ከሩ ህሩህነት ጋር የተያያዘ እንጂ ዝም ብሎ አባት ካልሆነ ለምን እግዚአብሔርን እፈራዋለሁ?» ሊሉ ይችላሉ::

እግዚአብሔር ርህሩህ አምላክ ሲሆን ይህን ርህሩነቱን ተጠቅመን ክብሩን ልንዘነጋ ይገባልን? ግርማውንና አባትነቱንስ ልንስረሳ ይገባልን? እንድንወደው፣ እንድንፈራውና ትዕዛዙን እንድንፈጽም ቁጡ መሆን አለበት እንዴት? ፍቅርን ምክንያት በማድረግ ክብሩን ከዘነጋን ይህ እውነተኛ ፍቅር ሊሆን ይችላል እንዴ?

አባታችን እስከሆነ ድረስ እኛን መቅጣት መብቱ አይደ ለም እንዴ? ቅጣቱን መፍራት የለብንም? «ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚና ገረውን ምክር ረስታችኋል:: ለመቀጣት ታገሡ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርጋችኋልና አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና «ያለቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም::» (ዕብ. 12:6-8) ይላል ቅዱስ ጳውሎስ::

ስለዚህ ከአባት ርህራሄ ብቻ ሳይሆን ቅጣትንም እንጠ ብቃለን:: ቅጣት ለእኛ ጠቃሚ እንደሆነ ማመን አለብን:፤ እግዚአብሔርን በመፍራትና ለእርሱ በመታዘዝ እንድናድግና እንድንኖር ያደርገናል::

www.ethiopianorthodox.org

«ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍ ራቸውም ነበር እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና እርሱ ግን ከቅድስ ናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል::» (ዕብ 12:9-10) ብሏል ቅዱስ ጳውሎስ::

ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔርን መፍራት ብዙዎች ተስ ማሚ አለመሆኑን ስለሚያውቅ «ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳ ዝነው እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ስለ መዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል::» (ዕብ 12:11) በማለት የጠቃልላል:: የእግዚአብሔር አባትነት ሲያሞ ላቀቀን አይደለም

ይልቁንም ሕይወታችን ተቀይሮ እንድንኖር ለቅጣት፣ ለስርአትና ለመገደብ ነው:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ያን ፍቅር ከፍርሀት ጋር ተቀላቀለ መሆን አለበት:፤ ቅዱስ ጳውሎስ በስጋ ስላሉ አባቶቻችን «ይቆጡን ነበር እኛም እንፈራቸው ነበር» ብሎ ተናግሯል:: እንፈራቸው ነበር ሲል አከብራቸውና እንታ ዘዛቸው ነበር ማለት ነው:: እንፍራ አለበለዚያ ግን ኃጢአትን እንሰራለን::

4 እንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔር በመልካምነቱና በደ ግነቱ የታወቀ ሆኖ ሳለ ለምን እንፈራዋለን? ሲሉ ይችላሉ::

ነገር ግን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና ሰውን መውደድ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ



ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም» (ቲቶ. 3:4-5) ይላል ቅዱስ ጳውሎስ::

ቅዱስ ጳውሎስ «...የእግዚአብሐርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት...» (ሮሜ 11:22) ብሏልና ስለ እግዚአብሔር ቸርነቱ ግን ፀንተህ ብትኖር የእግዚብሔርን ቸርነት በአንተ ላይ ነው ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ::» (ሮሜ 11:22) በማለት ይቀጥላል::

5 አንዳንዶች ግን እኮ እግዚአብሔር ታጋሽና መሀሪ ነው ሊሉ ይችላሉ::

እንደልጅና እንደአማኝ ኃጢአትን እየሰሩ ለመቀጠል የእግዚአብሔርን መሀሪነትና ታጋሽነት መጠቀም መልካም አይ ደለም:: «ወይስ የእግዚብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስህ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔርን ፍርድ በሚገለጽበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻህ:: እርሱ ለእያንዳንዱ እንደሥራው ያስረክበዋል» (ሮሜ. 2:4-6) እያለ የእግዚአብሔርን ታጋሽነት በመጠቀም ክፉ የሚሰሩትን ይነቅፋቸዋል::

የእግዚአብሔር ርህራሄ ሥርዓት አልበኝነትን አይፈቅ ድም:: ታጋሽ ነው ማለት ደግሞ ከኃጢአታችን ጋር ይስማማል ደግሞም አይቀጣንም ማለት አይደለም:: ከእግዚአብሔር ጋር አይጣጣምምና እግዚአብሐር ይህንን ነገር በጥብቅ ይቃወማል:: ንስሐ የምትገባበትን እድል እንድታገኝ ስለሚፈልግ እግዚአ ብሔር ልክ ኃጢአት በምትሠራ ሰአት አይቀጣህም::

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ የእግዚአብሔርን ትዕግስተኛነት መፍራት አለብን:: አለበለዚያ ግን የእግዚአብሔር ቁጣ ይሞላና ንስሀ የምንገባበትን እድል እናጣለን:: የፍርድንም ቀን እንጋፈጣለን:፤ (ሮሜ 2:21) በሙሴ ጊዜ እግዚአብሔር ፈርኦንን መታገሱ ፈርኦንን አይቀጣውም ማለት አይደለም:: አመፃቸው በወቅቱ ስላልሞላ እግዚአብሔር አሞራውያንን ታግሷቸዋል:: (ዘፍ. 15:16) የኃጢአታቸው ፅዋ በሞላ ጊዜ ለሙሴ አሳልፎ ሰጣቸው::

**6** «ውደድ ከዛ የፈለከውን አድርግ» የሚለውን የአውግስቲንን አባባል የሚጠቀሙ ተቃዋሚዎች ያሳዝኑናል::

በእርግጥ የፈለከውን ኃጢአትና መተላለፍ ፈጽም ማለት አይደለም:: ለእግዚብሔር ካለህ ፍቅር የተነሳ ለእግዚአብሔር የወደድከውን ነገር ማድረግ ትችላለህ ማለት ነው:: ስለዚህ በፍቅር ስም ነገሮችን በማይሆን መልኩ አትተርጉማቸው::